# ኢትዮ ቻምበር

ሚዲያ ጭማቂ

በኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት

በኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የኮሚኒኬሽንና ህዝብ ግንኙኙነት መምሪያ የሚዘጋጅ ወርሃዊ የሚድያ ጭማቂ

ህዳር 2014 ዓ.ም.



ቻይና ኢትዮጵያን ጨምሮ አፍሪካ - 2

ዓለም አቀፍ መንገደኞች በሻንጣ - 2

በጥቅምት ወር ከወጪ ንግድ - 2

ምርት ገበያው በአራት ወራት - 3

የውጭ ምንዛሪ አጠቃቀምን - 4

አዲሱ የውጭ ምንዛሪ አጠቃቀም - 4

ከኢትዮጵያ ጎን የቆሙ አጋር አገሮች - 5

የእስራኤል የማዕድን ኩባንያ - 5

ግብር ከፋዮች የታክስ ሕጎችን - 6

የሲሚንቶ ገበያ ሰንሰለት አሻጥር -6

ከ32.5 ቢሊዮን ብር በላይ የሚያወጣ - 6

ኢትዮጵያ የአጎዋን ዕድል ብትከለከልም - 7

የግብርና ምርቶች በአግባቡ የሚከማቹበትና - 7

የኢትዮጵያ አየር መንገድ አሸናፊ ሆነ- 7

የፈቃድ ብቃት ማረጋገጫ - 7

ረቂቅ ስትራቴጂ ለማፀደቅ -8

123 ቢሊዮን ብር ግብር -8

የቀዝቃዛ መጋዘን ለመገንባት- 8


## ተጥሎ የነበረው የብድር ዕግድ መነሳት ለባንኮችና ተበዳሪዎች መነቃቃት ፈጥሯል

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ከኢኮኖሚ አሻጥር፣ ከዋጋ ግሽበትና ተያያዥ ነገሮች ጋር በተያያዘ ባንኮች ብድር እንዳይሰጡ አስተላልፎት የነበረውን መመርያ በማንሳት፣ ለሁሉም የቢዝነስ ዘርፎች ብድር ማቅረብ እንደሚችሉ ማስታወቁ የኢኮኖሚው እንቅስቃሴ ላይ አዎንታዊ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ተገለጸ፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ኅዳር 20 ቀን 2014 ዓ.ም. ለባንኮች ባስተላለፈው መልዕክት፣ የብድር ክልከላው መነሳቱንና ባንኮች ለሁሉም ዘርፎች ብድር መስጠት እንደሚችሉ ማስታወቁ፣ በኢኮኖሚው ላይ አዎንታዊ ተፅዕኖ እንደሚኖረው እየተገለጸ ነው፡፡ የብድር ክልከላው መነሳቱን አስመልክቶ አስተያየታቸውን ለሪፖርተር የገለጹት የዳሽን ባንክ ፕሬዚዳንት አቶ አስፋው ዓለሙ፣ ላለፉት ሦስት ወራት ተግባራዊ ሆኖ የቆየው የብድር ክልከላ ባንኮች ላይም ሆነ የተለያዩ ቢዝነሶች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳርፎ እንደነበር ጠቅሰው፣ አሁን መፈቀዱ ኢኮኖሚው ላይ መነቃቃት ይፈጥራል ብለዋል፡፡ ብሔራዊ ባንክ የብድር ክልከላውን ተከትሎ ከባንኮችና ከተበዳሪ ደንበኞች እየቀረበ ያለውን አቤቱታ ከግምት በማስገባት፣ የተለያዩ የቢዝነስ ዘርፎች በተናጠል የብድር ጥያቄዎችን ማስተናገዳቸውን ሲያሳውቁ የነበረ ቢሆንም፣ በርካታ የብድር ጥያቄዎች ሳይስተናገዱ ቆይተው ነበር፡፡ ዕግዱ መነሳቱ ጥሩ መሆኑን ተናግረዋል፡፡ ሌላው የፋይናንስ ባለሙያ አቶ አሰግድ ገብረ መድኅን፣ ባንኮች ብድር እንዳይሰጡ ተግባራዊ ሲደረግ የነበረው መመርያ መነሳቱ ትልቅ ዜና ነው ይላሉ፡፡ ኢኮኖሚው እንዲነቃቃ ብቻ ሳይሆን በፋይናንስ እጥረት ቆመው የነበሩ ቢዝነሶች ሥራቸውን በተሻለ እንዲሠሩ ያስችላቸዋል፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ብድር እንዳይሰጡ በተላለፈው መመርያ መሠረት የተፈቀደ ብድር ሳይቀር እንዳይንቀሳቀስና እንዳይለቀቅ በመደረጉ፣ የተለያዩ ቢዝነስ ዘርፎች የሥራ እንቅስቃሴዎቻቸው ላይ ተግዳሮት ፈጥሮ እንደነበር ሲገለጽ መቆየቱም አይዘነጋም፡፡ አቶ አሰግድ እንደገለጹትም፣ ለየትኛውም የቢዝነስ እንቅስቃሴ ገንዘብ ወሳኝ ነው፡፡ ያለ ገንዘብ ምንም ማድረግ አይቻልም፡፡ መንግሥት ብድር እንዲቆም ማድረጉ በወቅቱ ከነበረው ሁኔታ አንፃር ትክክል ነው፡፡ አሁን ብድሩን መልቀቁ ደግሞ ኃላፊነቱን በሚገባ መወጣቱን ያሳያል ብለዋል፡፡

የብድር ክልከላው ተግባራዊ በነበረበት ወቅት ባንኮች ምን ያህል ተፅዕኖ ፈጥሮባቸዋል የሚል ጥያቄ የቀረበላቸው አቶ አስፋው፣ የባንኮች የሀብት መግለጫ ሚዛናቸውም ሆነ አጠቃላይ የባንክ እንቅስቃሴ ዋነኛ መሠረት ባንኮች የሚሰጡት ብድር ነው ብለው፣ ከአጠቃላይ ገቢያቸው ከፍተኛውን ድርሻ የሚያገኙት ከሚሰጡት ብድር በሚያገኙት ወለድ በመሆኑ፣ የብድር መቆም ገቢያቸው በከፍተኛ ሁኔታ እንዲቀንስ እንደሚያደርግ ገልጸዋል፡፡ ስለዚህ ብድር እንዳይሰጡ ተከልክለው መቆየታቸው ባንኮች ላይ ያሳደረው ጫና ከፍተኛ መሆኑን ያመለክታል በማለት፣ ክልከላው በባንኮች ገቢ ላይ የሚታይ ጫና ስለመፍጠሩ አስረድተዋል፡፡ ሌላው ደግሞ ባንኮች ብድር አቁመዋል በሚባልበት ጊዜ ኅብረተሰቡ ‹ብድር መቼ እንደማገኝ ስለማላውቅ፣ ያለብኝን ብድር በቅጣትም ቆይቼ እከፍላለሁ› በሚል ዕሳቤ ያለበትን ብድር እንዳይከፍል ማድረጉም ሊጠቀስ የሚገባው ተግዳሮት እንደነበር አክለዋል፡፡ ስለዚህ የብድር ክልከላው በብድር አመላለስ ላይም የራሱ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳርፎ እንደነበር አመልክተዋል፡፡ አሁን ብድር እንዲሰጥ መፈቀዱ ደግሞ በርካታ ጠቀሜታዎችን ይዞ ይመጣል ብለዋል፡፡

ባንኮች ብድር በሚሰጡበት ጊዜ ገንዘብ ይፈጥራሉ ያሉት አቶ አስፋው፣ በአንድ ባንክ የተሰጠ ብድር፣ ብድሩ ከዚያ ብቻ አይቀርም፣ ከሌላው ባንክ ደንበኛም ጋር ይደርስና ተቀማጭ ይሆናል፣ ተቀማጭ ያገኘው ባንክ ደግሞ ተጨማሪ ብድር ለመስጠት ዕድል ይሰጠዋል፡፡ ስለዚህ የገንዘብ መፍጠርና ማባዛቱ ሒደት ላይ አዎንታዊ ተፅዕኖ ይኖረዋል ብለዋል፡፡ የብድር ገደቡ መነሳቱ እንደተሰማ ከየአቅጣጫው እየታየ ያለው ስሜት የሚያመለክተው ነገር ያለ መሆኑን የጠቀሱት አቶ አሰግድ፣ የብድር ገደቡ በዚህ ወቅት መነሳቱ ከጦርነቱ ጋር በተያያዘ ሊከሰት ይችል የነበረውን ጉዳት እንዳይሰፋ በማድረግ ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳለውም ጠቁመዋል፡፡

መንግሥት ከገንዘብ ፖሊሲ አንፃር ይህንን ዕርምጃ ሲወስድ ለአገር ኢኮኖሚ የሚጠቅሙ ሁኔታዎችን መከላከል የፈለጋቸውን ነገሮች ከመከላከል አኳያ የተወሰዱ መሆኑን ያስታወሱት አቶ አስፋው፣ ከአገራዊ ሁኔታ አንፃር ዕርምጃው በመልካም የሚታይ መሆኑንም ሳይጠቅሱ አላለፉም፡፡ ገደቡ ስለተነሳ አሁን ወደ ሥራ መግባት የሚቻል ቢሆንም፣ ብድር እንዳይሰጥ መከልከሉ በመመርያ ደረጃ ተነገረ እንጂ፣ አንዳንድ ጊዜ ባንኮችም በቂ የሆነ ጥሬ ገንዘብ በማይኖርበት ሰዓት ላይ በፖሊሲ ደረጃ ባይከለከልም ብድሮችን የሚይዙበት ጊዜ እንዳለ መታወቅ አለበት ይላሉ፡፡

በግብር መክፈያ ወቅት ከጥቅምት ወር ጀምሮ ከፍተኛ ግብር ከፋዮች ግብር የሚከፍሉ ስለሆነ ሁልጊዜ ባንኮች በዚህ ጊዜ ውስጥ ከፍተኛ ጫና ይገጥማቸዋል፡፡ ስለዚህ ብድር መስጠት ይቻላል ሲባል የባንኮችም አቅም አብሮ መታየት እንዳለበት ጠቅሰዋል፡፡ እኛም ከዚህ አንፃር እንደምንረዳውና እንደምናየው ዛሬ ብድሩ ተፈቀደ እንበል እንጂ ብድር ተፈቀደ መባሉ ብድር እንደ ልብ ይሰጣል ማለት ላይሆን እንደሚችልም አቶ አስፋው ይገልጻሉ፡፡

ለዚህም እንደ ምክንያት የሚጠቀሱት ደግሞ በቅርቡ ተግባራዊ መሆን የጀመረው የብሔራዊ ባንክ አዲስ መመርያ መሠረት ባንኮች በብሔራዊ ባንክ ማስቀመጥ ያለባቸው የመጠባበቂያ የገንዘብ መጠን ከአምስት በመቶ ወደ አሥር በመቶ በማደጉ ይህንን መጠባበቂያ ገንዘብ ለማሟላት ገንዘባችንን በሙሉ ወደዚያ እናስገባ ስለነበር የገንዘብ እጥረት ሊኖር ስለሚችል ነው፡፡ በሌላ በኩልም ከግብር ክፍያ ጋር በተያያዘ የወጣ ገንዘብም ስለነበር እንደተፈለገ ብድር ይሰጣል አለማለት እንደሆነም ሳያመለክቱ አላለፉም፡፡ ሆኖም እንዲህ ያለውን ጫና፣ አካክሰን ወደ ብድር የምንገባበት ሒደት እንፈጥራለን ብለዋል፡፡ እንደፈለግነው ባይሆንም ግን ብድር መስጠቱ እንደሚቀጥ ገልጸዋል፡፡ በጥቅል ሲታይ ግን ብድር ክልከላው መነሳቱ ለኢንዱስትሪውም፣ ለባንክ ደንበኞችም ሆነ በአጠቃላይ ለኢኮኖሚው መልካም እንደሆነ አመልክተዋል፡፡ የአቶ አስፋው ሌላ ምልከታ ደግሞ ብድር ክልከላው መነሳቱ ብቻ በቂ አለመሆኑን ነው፡፡ ይህንንም፣ «የብድር ገደቡ አንድ ነገር ሆኖ፣ ብድር ለመስጠት ከዚህ መመርያ ጋር በተመሳሳይ ወቅት የወጣው ቋሚ ንብረቶችን ለማስያዣነት መጠቀም የማይችል መሆኑን የሚደነግገው መመርያ ጉዳይ መታየት አለበት፤» ይላሉ፡፡ ይህ መመርያ አብሮ ካልተስተካከለ ባንኮች ብድር ለመስጠት የሚቸገሩ ስለመሆኑም ጠቅሰዋል፡፡

«ብድር በምንሰጥበት ጊዜ እንደ ቤት ያሉ ቋሚ ንብረቶችን አስመዝግበን ነው፡፡ ከዚሁ መመርያ ጋር የወጣው ቋሚ ንብረትን ለብድር ማስያዝ መመርያ ስለመነሳቱ የተነረ ነገር የለምና ይህም መታየት አለበት፤» ያሉት አቶ አስፋው፣ ነገር ግን ብድር ኖሯቸው ኦቨር ድራፍታቸውን ለመጠቀም ወይም ደግሞ ያልተላቀቀ ብድር ኖሯቸው ሒደት ላይ ያሉና ለመሳሰሉት ግን ብድሩ ይለቀቃል ብለዋል፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://ethiopianreporter.com/article/23929

## የውጭ ኩባንያዎቹ የኢትዮጵያን ሕዝብና መንግሥት አምነው መምጣታቸውን አሁንም አላቋረጡም

ቀጥታ የውጭ የኢንቨስትመንት የውጭ ምንዛሪ ግኝትን ከፍ በማድረግ፣ ለቴክኖሎጂና ለእውቀት ሽግግር እንዲሁም ለዜጎች ሰፊ የሥራ ዕድል በመፍጠር ያለው አበርክቶ እጅግ ከፍተኛ በመሆኑ ለአገር ኢኮኖሚ ዕድገት ጉልህ ሚና ይጫወታል።

በምጣኔ የሀብት እድገታቸው የሚጠቀሱ አገሮችም የእድገታቸው ሚስጥር ከሆነው አንዱ ቀጥታ የውጭ ኢንቨስትመንትን መሳብ እንደሆነ ይታወቃል። በዚህ ረገድ በውጤታማነት ከሚጠቀሱ አገራት መካከል ቻይና ሲንጋፖር አንዷ ናት።

የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት የአገር ውስጥ ባለሀብቶች የተገኘውን ተሞክሮና የቴክኖሎጂ ሽግግር ተቀብለው በመተግበር እራሳቸውንም ሆነ አገርንም ተጠቃሚ ማድረግ ሲችሉ ደግሞ ውጤታማነቱ የበለጠ እንደሚሆን የተለያዩ መረጃዎች ያመለክታሉ። ኢትዮጵያም ቀጥታ የውጭ ኢንቨስትመንትን በመሳብ ኢኮኖሚያዊ እድገቷን ከፍ ለማድረግ መንቀሳቀስ ከጀመረች አመታት ተቆጥሯል።

ቀጥታ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ የተቀመጠውን መስፈርት ከማሟላቷ በተጨማሪ በተለያየ የኢንቨስትመንት ዘርፍ ለመሰማራት ለሚፈልጉ ባለሀብቶች ምቹ ሁኔታ መፍጠር መቻሏም ተመራጭ ያደርጋታል።



በኢትዮጵያ በቀጥታ የኢንቨስትመንት ተሳትፎ በማድረግ ቻይና፣ ህንድና ሆላንድ በግንባር ቀደምትነት ቢጠቀሱም የአሜሪካን ትላልቅ ኩባንያዎች መሳተፋቸውም አይዘነጋም። የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ አንዲት አገር የተረጋጋ ሠላምና ፀጥታ ሊኖራት ይገባል።

ከቦታ ቦታ እንቅስቃሴን በመገድብ፣ ንክኪን በመከልከል፣

(ወደ ገፅ 3 ዞሯል)

## ቻይና ኢትዮጵያን ጨምሮ አፍሪካ ውስጥ አሥር ቢሊዮን ዶላር ኢንቨስት ልታደርግ መሆኑን አስታወቀች



የቻይና መንግሥት ኢትዮጵያን ጨምሮ በሁሉም አፍሪካ አገሮች የአሥር ቢሊዮን ዶላር ኢንቨስትመንት ፈሰስ ለማድረግ ማቀዱን አስታወቀች። የቻይና ፕሬዚዳንት ሺ ጂንፒንግ በሴኔጋል ዋና ከተማ ዳካር ለሁለት ቀናት የተካሄደውን የአፍሪካ ቻይና ጉባዔ በቪዲዮ በከፈቱበት ወቅት እንደተናገሩት፣ አገራቸው የአፍሪካ አገሮች ኢኮኖሚ እንዲያገግም ይህንን ጨምሮ የተለያዩ መዋዕለ ንዋዮችን ለማፍሰስ ዝግጁ ናት።

የገንዘብ ሚኒስቴር ከፍተኛ ሥራ ኃላፊዎች ኢትዮጵያን ወክለው በተገኙበት ጉባዔ ላይ፣ በአፍሪካ አገሮች ያለውን ድህነት ለመቀነስና የግብርና ዘርፉን ለማዘመን 500 የግብርና ባለሙያዎችን ወደ አኅጉሪቱ ለመላክ ማቀዳቸውን ፕሬዚዳንቱ አስታውቀዋል። በተጨማሪም እንደ ኢትዮጵያ ያሉ የግብርና ምርት ላኪዎችን ይጠቅማል የተባለ ማሻሻያ ይፋ ያደረጉ ሲሆን፣ ይህም የግብርና ምርቶችን ያለ ቀረጥ ኢትዮጵያ ወደ ቻይና እንድትልክ ይረዳታል ተብሏል።

በአዲሱ ማሻሻያ መሠረት ማንኛውም ከቻይና መንግሥት ጋር የዲፕሎማቲክ ግንኙነት ያላቸው አገሮች ከቀረጥ ነፃ የሚያስገቧቸው ምርቶችን ብዛት የሚጨምሩ ሲሆን፣ ቻይና በየዓመቱ ከአፍሪካ አገሮች የምታስገባቸውን ምርቶች አሁን ካለበት 210 ቢሊዮን ዶላር ወደ ግማሽ ትሪሊዮን ዶላር ያሳድጋል ተብሎ ይጠበቃል።

በተጨማሪ ቻይና ይዛው የመጣችው አዲስ ማሻሻያ ምንም እንኳን ተግባራዊ ባይደረግም፣ ኢትዮጵያ ከአሜሪካ የቀረጥ ነፃ ተጠቃሚነት ዕድል ከተሰረዘች ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ መሆኑ፣ የገበያ አማራጭ ከማምጣት አኳያ ትልቅ ሚና ይጫወታል ተብሎ ይጠበቃል።

የጠቅላይ ሚኒስትር ዓብይ አህመድ (ዶ/ር) ከፍተኛ አማካሪ አቶ ማሞ ምሕረቱ፣ ‹‹ቻይና የወሰደችው ዕርምጃ ተገቢና ጊዜውን የጠበቀ ነው፤›› በማለት ያደነቁ ሲሆን፣ ‹‹ለኢትዮጵያ ትልቅ ዜና ነው፤›› ብለዋል።

አቶ ማሞ ቻይና ይፋ ያደረገችው ማሻሻያ ትልቅ ገበያ ለኢትዮጵያ እንደሚፈጥር ለሪፖርተር ገልጸው፣ ‹‹ኢኮኖሚያችንን ወይም ዘርፎችን እንድንከፍት የማያስገድድ መሆኑ የበለጠ የገበያ ዕድል ይከፍታል፤›› ብለዋል።

በተመሳሳይ የኢንቨስትመንት አማካሪና የፋይናንስ ባለሙያው አቶ ዘመዴነህ ንጋቱ፣ ‹‹ይፋ የተደረገው የዜሮ ታሪፍ ፖሊሲ በአገዋ ይላኩ የነበሩ ምርቶች ወደ ቻይና ለመላክ ዕድል ይከፍታል፤›› ያሉ ሲሆን፣ ይህም በአሥር ሺሕ የሚቆጠሩ ሠራተኞችን ከማዳን አኳያ ትልቅ ሚና ይኖረዋል ብለዋል።

በተቻለ አቅም በፍጥነት እንዲተገበር መንግሥት ይፈልጋል ያሉት አቶ ማሞ በበኩላቸው፣ የቀረጥ ነፃ ዕድሉ ከግብርና ምርቶች በተጨማሪ በፋብሪካ የተመረቱ ዕቃዎችን ቢያካትት መልካም ነው ሲሉ ሐሳባቸውን አጋርተዋል።

በሌላ በኩል አሥር ቢሊዮን ዶላር ብድር በቀጣይ ሦስት ዓመታት ለአፍሪካ አገሮች አቀርባለሁ ያለችው ቻይና፣ ከአፍሪካ አገሮች የበለጠ የግብርና ምርቶች ለመግዛት እንዲያስችላት የተለያዩ መሠረት ልማቶች ለማሟላት ማቀዷን ይፋ አድርጋለች። ‹‹የአፍሪካ አገሮች የብድር ወጥመድ ውስጥ እንዲገቡ በማድረግ በቁጥጥሯ ሥር እንዲወድቁ ታደርጋለች›› የሚል ወቀሳ በአሜሪካ መንግሥት በተደጋጋሚ የቀረበባት ቻይና፣ በዳካር በነበረው ስብሰባ ላይ ለአፍሪካ አገሮች የብድር ምሕረት ለማድረግ ማሰቧን አስታውቃ ነበር።

ኢትዮጵያ ከውጭ አበዳሪዎች ከወሰደችው ከ29 ቢሊዮን ዶላር ብድር ውስጥ ከአንድ ሦስተኛ በላይ የሚሆነው ከቻይና አበዳሪዎች የወሰደችው ሲሆን፣ በቅርቡ የመክፈያ ጊዜ ማራዘሚያ እንዲደረግላት በቡድን 20 አገሮች በኩል ማቅረቧ ይታወሳል። በተጨማሪ ቻይና ኢትዮጵያ ከውጭ ከምታስገባቸው ምርቶች ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ ያላት ሲሆን፣ በየዓመቱ ከሚገባው 13 ቢሊዮን ዶላር ከሚጠጋ ምርት ውስጥ ድርሻዋ 25 በመቶ አካባቢ ይሆናል።

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://ethiopianreporter.com/article/23923

## ዓለም አቀፍ መንገደኞች በሻንጣ የሚያስገቧቸው ዕቃዎች ላይ ክልከላ መጣሉ እያወዛገበ ነው

ዓለም አቀፍ መንገደኞች በሻንጣ የሚያስገቧቸው ዕቃዎች ላይ ክልከላ መጣሉ እያወዛገበ ነው

ከኅዳር 25 ቀን 2014 ዓ.ም. ጀምሮ ተግባራዊ የተደረገው፣ ተመላላሽ ነጋዴዎች ያለ ምንም ቀረጥ የግል መገልገያ ዕቃዎች ማስገባትን የሚከለክለው አዲሱ አሠራር ማወዛገቡን ቀጥሏል።

የዓለም አቀፍ መንገደኞች ከውጭ ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ፣ እንደ ልብስና ጫማ ያሉ የግል መገልገያ ዕቃዎችን ማስገባት ይፈቅድ የነበረው መመርያ አፈጻጸም ላይ ዕግድ ያስቀመጠው አዲሱ አሠራር፣ በጉምሩክ ኮሚሽን ትዕዛዝ የተተገበረ ሲሆን፣ ሕገወጥ ንግድን ለማስቀረት ያለመ ነው።

አዲሱ ክልከላ ቱሪስቶችን፣ ዲፕሎማቶችን እንዲሁም ተመላላሽ ያልሆኑ መንገደኞች የግል መገልገያ ዕቃዎቻቸውን ማስገባት ባይከለክልም የሚያመጧቸው ዕቃዎች አዳዲስ ከሆኑ ቀረጥና ታክስ እንዲከፍሉ ያስገድዳል።

ምንም እንኳን የጉምሩክ ኮሚሽን ዕርምጃው ግብር የሚከፍሉ ነጋዴዎች የሚያበረታታና ሕጋዊ አስመጪዎችን ከኪሳራ የሚያድን ነው ቢልም፣ በዘርፉ የተሰማሩ ነጋዴዎችና ባለሙያዎች ውሳኔውን ተቃውመዋል።

ሪፖርተር ያነጋገራቸውና ከአምስት ዓመታት በፊት ወደ ችርቻሮ ንግድ የገባው አቶ ኪሩቤል (የአባቱ ስም እንዳይገለጽ የጠየቀ) መጀመርያ የአገር ውስጥ ጫማዎችን ይነግድ እንደነበር ይናገራል፡፡

መገናኛ አካባቢ በግምት 20 ካሬ ላይ ያረፈ ጫማ ቤት ተከራይቶ ሥራ የጀመረው ኪሩቤል፣ ንግድ የጀመረ ሰሞን ትርፋማ የነበረ ቢሆንም የውጭ አልባሳትና ጫማዎችን የሚሸጡ ሱቆች በሚሠራበት አካባቢ ቁጥራቸው በመጨመሩ መተው የሚገዙ ቀርቶ በደጃፉ የሚያልፉ ሸማቾች ሳይቀር እንደጠፉና ከዓመት በኋላ ዘርፍ ለመቀየር መገደዱን ያወሳል።

ዘርፉን በመቀየር ፒያሳ አካባቢ ከአራት ዓመታት በፊት ሱቅ የከፈተው ኪሩቤል የንግድ እንቅስቃሴው ከሞላ ጎደል ጥሩ እንደነበር ይናገራል፡፡

በየዓመቱ ያለበትን የገቢ ግብር እንደሚከፍል የሚገልጸው አቶ ኪሩቤል፣ በየወሩ ከ30 ሺሕ ብር በላይ ተጨማሪ እሴት ታክስ ለመንግሥት ሰብስቦ ያስረክባል።

የተለመደ ሥራውን እየሠራ ግዴታውንም እየተወጣ መሆኑን የሚገልጸው አቶ ኪሩቤል፣ ተመላላሽ ነጋዴዎችን አስመልክቶ የወጣውን አዲሱ የጉምሩክ አሠራርን ከሰማ አንስቶ እንቅልፍ ማጣቱን ይናገራል፡፡

ከሚሸጣቸው ምርቶች ውስጥ ከ75 በመቶ በላይ የሚሆነውን ከተመላላሽ ነጋዴዎች የሚያገኘው ኪሩቤል ‹‹አዲሱ አሠራር መሬት ላይ ያለውን እውነታ ያላገናዘበ ነው›› ይላል።

በከተማ ያሉ ቸርቻሪዎች ከሚሸጡት አልባሳትና ጫማ ውስጥ ከፍተኛ ድርሻውን ከተመላላሽ ነጋዴዎች እንደሚያገኙና ለዚህም ዋነኛ ምክንያቱ አስመጪዎች ምርቶችን ከውጭ ሲያመጡ ጥራት ላይ ስለማያተኩሩ፣ ሸማቾች ትኩረት የሚያደርጉት ጥራት ላይ መሆኑን የሚያሳይ ከመሆኑ አንፃር ውሳኔው ተገቢ አለመሆኑን ተናግሯል፡፡

ችግሮቹ ሳይፈቱ ተመላላሽ ነጋዴዎች ላይ ዕገዳ ማስቀመጡ ተገቢ አለመሆኑን የሚሞግተው አቶ ኪሩቤል፣ የውሳኔው አሉታዊ ተፅዕኖ ከወዲሁ እየታየ መምጣቱን ያነሳል። ለዚህም አዲሱ አሠራር በተገበሩ በሦስት ቀናት ውስጥ የገጠመውን ያነሳል።

‹‹ገና ውሳኔው በተሰማ ቀናት ውስጥ በመርካቶ የሚገኙ አስመጪዎች ከውጭ የሚመጡ ጫማዎች ላይ ከ1,200 ብር ላይ ጭማሪ አድርገዋል›› ሲል ወቀሳውን የሰነዘረው አቶ ኪሩቤል ‹‹ከሳምንት በፊት በጅምላ 2,000 ብር ይሸጡ የነበሩ ጫማዎች 3,000 ብር እንደገቡ›› ይናገራል። ይህም የክልከላው ውጤት ነው ሲል ወቀሳውን ጉምሩክ ኮሚሽን ላይ ሰንዝሯል።

አስመጪዎች በዚህ ሐሳብ አይስማሙም። በተደጋጋሚ ለጉምሩክ ኮሚሽንና ለፋይናንስና የገቢዎች ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች ባቀረቡት ቅሬታ የተመላላሽ ነጋዴዎች መብዛት ተወዳዳሪ እንዳላደረጋቸውና በዚህም የተነሳ ገበያው ላይ መፎካከር እንዳልቻሉ ሲገልጹ ቆይተዋል።

ተመላላሽ ነጋዴዎች ከሃዋላ የሚገኝ ገንዘብን ከትይዩ ገበያዎች በመግዛታቸው የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት ይወስድባቸው የነበረውን ጊዜ እንዳረዘመባቸው በተደጋጋሚ ሲናገሩ ይሰማል።

የምጣኔ ሀብት ባለሙያ የሆኑት አቶ ጥሩነህ አሰፋ ውሳኔው ከሚደግፉት መካከል ናቸው። ለዚህም ሁለት ምክንያቶች ያነሳሉ።

በውሳኔው ለመደገፋቸው እንደ መጀመርያ ምክንያት የጠቀሱት ተመላላሽ ነጋዴዎች በአልባሳቶች ላይ ለታየው ዋጋ ግሽበት ያደረጉት አስተዋጽኦ ሲሆን፣ በተለይም በተለያዩ አገሮች በሚጓዙበት ወቅት ለመኝታና ትራንስፖርት የሚያወጡት ወጪ ከሚያመጡት ዕቃዎች መጠን አነስተኛ ከመሆኑ ጋር ተዳምሮ፣ ወጪያቸውን ለመሸፈን የሚያስገቡትን ዕቃ በውድ ዋጋ በመሸጥ የዋጋ ግሽበት መፍጠራቸውን ይገልጻሉ፡፡

ነገር ግን እንደ ባለሙያው ገለጻ በሕጋዊው መንገድ በመርከብ አስጭነው የሚያስመጡ ነጋዴዎች የሚያመጡት ዕቃዎች ብዙ ስለሆነ በዋጋው አኳያ በተመጣጣኝ መልኩ ምርቶችን ማከፋፈል እንደሚችሉ ያነሳሉ። ጉምሩክ ኮሚሽንም ሕጋዊ አስመጪዎችን ለመደገፍ ተመላላሽ ነጋዴዎች መከልከሉ ትክክለኛ ውሳኔ ነው ይላሉ።

የተለያዩ ድርጅቶችን በመምራት ከ15 ዓመት በላይ ልምድ ያካበቱት የቢዝነስ አመራር ምሩቁ አቶ ፍፁም ደምሴ በዚህ ሐሳብ አይስማሙም።

የተመላላሽ ነጋዴዎች የሚያገለግሉት መካከለኛና ከፍተኛ ገቢ ያላቸው ዜጎችን መሆኑን የሚገልጹት አቶ ፍፁም፣ አስመጪዎች ምርቶችን ከቻይና በብዛት እንደሚያመጡ በመጥቀስ የሚያገለግሉት አነስተኛ አቅም ያላቸውን ሸማቾች እንደሆነ ገልጸዋል።

‹‹አስመጪዎች በተመላላሽ ነጋዴዎች አይጎዱም›› ሲሉ የሚሞግቱት አቶ ፍፁም፣ ዕርምጃው ሥራ እጥነት ሊያስፋፋ እንደሚችልም ጠቁመዋል፡፡

መንግሥት ከግብር ባለፈ የተመላላሽ ነጋዴዎች ሁኔታ መመልከት እንዳለበትና ብዙኃኖቹም ሴቶችና የዩኒቨርስቲ ምሩቆች እንደሆኑም አክለዋል፡፡

በተመሳሳይ ከዚህ ቀደም የተቃዋሚ ፓርቲ መሪ የነበሩትና በሙያቸው የፋይናንስ ባለሙያ የሆኑት አቶ ሙሼ ሰሙ ውሳኔውን የተቃወሙ ሲሆን፣ ከሻንጣ ንግድ ዋነኛ ተጠቃሚ የኢትዮጵያ አየር መንገድ መሆኑን በመጥቀስ፣ አገሪቷ ፈታኝ ሁኔታ ውስጥ ባለችበት ወቅት ዕግዱ ተግባራዊ መሆኑ ኢመደበኛ ለፍቶ አዳሪዎችን እንደሚጎዳ በማኅበራዊ ትስስር ገጻቸው ባሰፈሩት ጽሑፍ ሞግተዋል።

ዜጎች ለዕርዳታ ተቀባይነትና ለማኅበራዊ ቀውስ እንዳይዳረጉ ሲባል ኢመደበኛ ሥራዎችን ቢቻል ከግብር ነፃ በማድረግ ወይም በዝቅተኛ ታክስ ሠርተው የመኖር ዕድል ሊነፍጋቸው አይገባም ሲሉ ሞግተዋል።

የጉምሩክ ኮሚሽን ሥራ ኃላፊዎች ተግባራዊ የተደረገው ዕግድ ትክክለኛ ውሳኔ መሆኑን ያነሳሉ። በሕጋዊ መልኩ ከውጭ ምርቶችን የሚያስገቡ ነጋዴዎችን ያበረታታል ይላሉ። የጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር የሆኑት አቶ ደበሌ ቃበታ የሚያነሱትም ተመሳሳይ ምክንያት ነው። እንደ ኮሚሽነሩ ገለጻ ተመላላሽ ነጋዴዎች ከጅምሩ አንስቶ ያደርጉት የነበረው የንግድ እንቅስቃሴ በመመርያ የተፈቀደ አልነበረም፡፡ በመሆኑም ዕቃዎችን ከውጭ እያስመጡ መሸጣቸው ሕገወጥ ነበር ብለዋል፡፡

ይሁን እንጂ በመመርያው ላይ የነበረውን ክፍተት በመጠቀም ከሌሎች ተጓዦች ጋር በመመሳሰል ምርቶቹን ያስገቡ ነበር የሚሉት አቶ ደበሌ፣ ዕግዱ ሕገወጦችን ለመለየት ትልቅ ሚና ይጫወታል ብለዋል።

እሳቸው የሚመሩት ኮሚሽንም አዲሱ አሠራር የማይተገብሩ ተመላላሽ ነጋዴዎች ለመጀመርያ ጊዜ ከሆነ ቀረጥ ከፍለው እንዲገቡ በድጋሚ ይህን መሰል ተግባር ላይ ከተገኙ በወንጀል ጉዳያቸው እንደሚታይ አስጠንቅቋል።

እነዚህ ተመላላሽ ነጋዴዎች ከፈለጉ በሕጋዊ መንገድ ሌተር ኦፍ ክሬዲት (ኤልሲ) ከፍተው በመሥራት ይህን መሰል ከሆነ ችግር መዳን እንደሚችሉ አቶ ደበሌ ለሪፖርተር ገልጸዋል፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://ethiopianreporter.com/index.php/article/23999

## በጥቅምት ወር ከወጪ ንግድ 311 ነጥብ 5 ሚሊን ዶላር ገቢ ተገኘ

በጥቅምት ወር ከወጪ ንግድ 311 ነጥብ 5 ሚሊን ዶላር ገቢመገኘቱን የኢትዮጵያ ንግድና ቀጠናዊ ትሥሥር ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

ከጥቅምት ወር ወጪ ንግድ 358 ነጥብ 9 ሚሊየን ዶላር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 311 ነጥብ 5 ሚሊየን ዶላር ገቢ መገኘቱን ገልጿል፡፡ ፈጻጸሙም 86 ነጥብ 80 በመቶ መሆኑን ነው ከሚኒስቴሩ ያገኘነው መረጃ ያመላከተው፡፡

የግብርናው ዘርፍ 205 ነጥብ 9 ሚሊየን ዶላር ገቢ በማስገኘት ትልቁን ድርሻ የያዘ ሲሆን÷ የኢንዱስትሪ ዘርፍ 39 ነጥብ 6 ሚሊየን፣ የማዕድን ዘርፍ 58 ነጥብ 5 ሚሊየን እንዲሁም ከኤሌክትሪክና ሌሎች 7 ነጥብ 54 ሚሊየን ዶላር ገቢ ማግኘት መቻሉ ተመላክቷል፡፡

የወጪ ንግድ ገቢውን ለማሳደግ የሚያስችሉ ስራዎች እየተሰሩ እንደሚገኝም ተጠቁሟል፡፡

ወደ ዘመናዊ ወጪ ንግድ የሚገቡ የምርት ዓይነቶችን ማሳደግ፣ የገበያ መዳረሻዎችን ማሳደግ እና የሁለትዮሽ ንግድ ግንኙነቶችንና ድርድሮችን በማካሄድ የመዳረሻ ገበያዎችን ማስፋት እየተሰራባቸው ያሉ ስትራቴጂክ የትኩረት መስኮች ነቸውም ነው የተባለው፡፡

የወጪ ንግድ ገቢውን ለማሳደግ አምስት ምርቶችን ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ ግብይት ሥርዓት እንዲሁም ሰባት የምርት አይነቶችን ደግሞ ወደ ውል አስተዳደር ሥርዓት ለማስገባት እየተሰራ መሆኑም ተገልጿል፡፡

አጎዋን የሚተካ አማራጭ ገበያ ማፈላለግ፣ የውል እርሻ መረጃዎችን ማጥራት፣ የምርት ነፃ እንቅስቃሴን የሚያደናቅፉና የዋጋ ንረትን የሚያስከትሉ ኬላዎችን ህጋዊ ሥርዓት እንዲይዙ ማድረግ፣ የህገ-ወጥና የኮንትሮባንድ ንግድን መከላከል፣ የግብይት ሥርዓቱን የአሠራር ሥርዓት መቅረጽና ተግባራዊ ማድረግ እንዲሁም ለክልሎችና ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮዎቸ እና ተጠሪ ተቋማት የኤክስፖርት ክትትል እንዲያደረጉ ማድረግ በቀጣይ ትልቅ ትኩረት ተሠጥቶ የሚሰራባቸው ጉዳዮች መሆናቸውም ተመላክቷል፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://www.fanabc.com/በጥቅምት-ወር-ከወጪ-ንግድ-311-ነጥብ-5-ሚሊን-ዶ/

## ተጥሎ የነበረው የብድር ዕግድ ... (ከገፅ 1 የዞረ)

ሰፊ ቁጥር ያለው የሰው ኃይልንም ለማሰማራት የማያስችል ብዙ ገደቦች ያለው ኮቪድ-19 ቫይረስ ወረርሽኝ በሽታም ኢንቨስትመንቱ እንዳይሳለጥ በማድረግ ተጽእኖ ያሳድራል። ኮቪድና የፀጥታ መጓደል በኢትዮጵያ ቀጥታ የውጭ ኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ላይ በመጠኑም ቢሆን ተጽእኖ ማሳደሩ አልቀረም።

ጫናው አሸባሪው ሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ(ትህነግ) በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል የከፈተው ጦርነት ብቻ ሳይሆን፣ ከትህነግ ድርጅት ጋር ሆነው የኢትዮጵያን ጥቅም ሲጋፉ የነበሩ እንደነአሜሪካን እና አንዳንድ ምእራባዊያን አገራትም አብረው በማበር ኢንቨስትመንትን በማዳከም የኢኮኖሚ ጫና ጦርነት ከፍተውባታል። ኢኮኖሚዋ እንዲደቅ የተለያዩ ማእቀቦችን በመጣል ሰፊ ዘመቻ ከፍተው እየተንቀሳቀሱ ይገኛሉ። እንደነርሱ እሳቤ ኢትዮጵያ የሕልውና ዘመቻ ላይ በመገኘቷ ማእቀቡ ሲበረታባትና ኢኮኖሚዋ ሲደቅ እጅ ትሰጣለች።

ምእራባዊያኑ በእጅ አዙር ቅኝ ለመያዝ የሚያደርጉት ጥረት ግን እንዳሰቡት አልሆነላቸውም። ኢትዮጵያ በጦርነቱም ቢሆን የበላይነቱን ይዛለች። በውጭ ኃይላት አይዞህ በርታ እየተባለ በጦርነቱ እየገፋበት ያለው ትህነግም ዋጋ እየከፈለ ይገኛል። ኢትዮጵያ ግን ኢኮኖሚዋን ለማዳከም እየተደረገባት ያለውን ጫና ተቋቁማ ጦርነቱን ኢኮኖሚው ተሸክሞት እንዲቀጥል ውጤት በማስመዝገብ ላይ ትገኛለች።

በሕልውና ዘመቻ እና በየጊዜው መልኩን እየቀያየረ ዓለምን እያስጨነቀ በሚገኘው ኮቪድ- 19 ወረርሽኝ ጫና ውስጥ ሆና የቀጥታ የውጭ ኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዋ በምን ደረጃ ላይ ይገኛል? በኢኮኖሚውም ቢሆን ከዚህ በኋላ አማራጭ የለም በሚል በምታደርገው ሁለተናዊ ጥረት የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት አንዱ በመሆኑ ኢንቨስትመንትን በመሳብ ስላለው ነባራዊ ሁኔታ ከኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የፕሮሞሽንና ፖሊሲ ጥናት ዘርፍ ምክትል ኮሚሽነር ተመስገን ጥላሁን ጋር ቆይታ አድርገናል።

እርሳቸውም ከአገራዊ ለውጡ በኋላ ያለውን የውጭ ቀጥተኛ የኢንቨስትመንት ፍሰትና ያለውን ነባራዊ ሁኔታ እንደሚከተለው አብራርተዋል። እንደ አቶ ተመስገን ማብራሪያ፤ ኢትዮጵያ በአፍሪካ ደረጃ የተሻለ የኢንቨስትመንት ፍሰት አላት ወይንም ለኢንቨስትመት ፍሰት ተመራጭ ናቸው ከሚባሉ አገራት መካከል አንዷ ስትሆን፣ በተለይም እአአ በ2017 እስከ አራት ነጥብ አንድ ቢሊየን ዶላር አገር ውስጥ ገብቷል።

የውጭ ኢንቨስተሮች ኢትዮጵያን በተለያየ መንገድ ይፈልጓታል። ከአፍሪካ ጋር ያላት ተወዳዳሪነትም በብዙ መለኪያዎች ይጠቀሳሉ። ኢትዮጵያ በመልክአ ምድሯ ትልቅ አገር ናት። እንደስፋቷም የተለያዩ እምቅ የተፈጥሮ ሀብቶች አሏት።

በወጣትነት እድሜ ላይ የሚገኝ የሚሰራ የሰው ኃይል ባለቤትም ናት። ከተለያዩ አገራት ጋር ያላት የዲፕሎማሲ ግንኙነትና የተረጋጋ የፖለቲካ እንቅስቃሴ የሰፈነባት መሆኗ በሌሎችም መዋእለ ነዋያቸውንና ያላቸውን ቴክኖሎጂ ይዘው ኢትዮጵያ ውስጥ ለመስራት ከተለያዩ አገራት የሚመጡ የውጭ ኩባንያዎች በርካታ ናቸው።

ያለፉትን የሶስት አመታት የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ መለስ ብለን ብንቃኝ ጥሩ ማሳያ ይሆናል። የ2010፣2011፣2012 ዓ.ም የነበሩት እንቅስቃሴዎች ከ2009ዓ.ም ከነበረው በተወሰነ ደረጃ የቀነሰበት ዘመን ነበር። በተለይም በ2012 ዓ.ም ከአራት ነጥብ አንድ ቢሊየን ዶላር ወደ ሁለት ነጥብ ሰባት ቢሊየን ዶላር ዝቅ ያለበት ወቅት ነበር። ይሄ ግን በዚሁ አልቀጠለም።

ሥራዎች በመሰራታቸው መሻሻል እየተመዘገበ ነው የመጣው። ከቀደሙት አመታት በተሻለ በ2013ዓ.ም ከፍተኛ እመርታ ማስመዝገብ ተችሏል። ወደ ሶስት ነጥብ ዘጠኝ ሰባት ቢሊየን ዶላር ከውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ማግኘት ተችሏል። ይህ ውጤት የተገኘው ዓለምን ለቀውስ የዳረገው ኮቪድ-19 ወረርሽኝ እና ኢትዮጵያ በውስጥ ጦርነት፣ ሌላው ዓለም ደግሞ የኢኮኖሚ ጫና ወይንም ጦርነት ከፍቶባት ባለበት ወቅት ነው።

ከተሰሩት አንኳር ሥራዎችና ውጤት ከተመዘገበባቸው ውስጥም አዲስ የቴሌኮም የንግድ ፈቃድ መስጠት ይጠቀሳል። ይህም ኢትዮጵያ በኢንቨስትመንት ዘርፍ ያላትን አቅም ማሳያ ነው ። ምንም እንኳን ኢትዮጵያ በውስጥ በተከፈተባት ጦርነት የሕልውና ዘመቻ ላይ ብትሆንም ታላቅ አገር መሆኗ አለመዘንጋቱን ያሳያል። የውጭ ኩባንያዎቹ የኢትዮጵያን ሕዝብና መንግሥት አምነው መምጣታቸውን አሁንም አላቋረጡም። እየመጡ እየሰሩ ይገኛሉ።

ሌላው መዘንጋት የሌለበት በአገር ደረጃ የተደረገው የኢኮኖሚ ለውጥ(ሪፎርም) የፈጠረው እድል በቀላሉ መታየት የለበትም። ለውጡ ለንግድና ኢንቨስትመንት የተለያዩ ነገሮችን አመቻችቷል።ቀደም ሲል ግን ኢትዮጵያ ለነዚህ ነገሮች ምቹ እንዳልሆነች ነበር የሚታሰበው። ለውጡ ይሄን ማስቀረት ችሏል። በለውጡ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ኢንቨስትመንትን የሚያበረታታ ለውጥ ተደርጓል።

ለአብነትም የኢትዮጵያን የንግድና ኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ለዘርፉ ተዋንያን ወይንም በዘርፉ ላይ ለሚገኙ አካላት ምቹ ማድረግም ያለፉት ሁለት ዓመታት የተደረጉ የለውጥ ሥራዎች አንዱ ማሳያ ሲሆን፣ በተሰራው ሥራም ለውጥ ተገኝቷል።

ለኢንቨስትመንትና ንግድ አሰራር አስቸጋሪ የሆኑ ከ80 በላይ የሚሆኑ ሕጎችና አሰራሮች እንዲለወጡ በማድረግ ሰፊ ሥራ ተሰርቷል። የአገልግሎት አሰጣጥ ሥርአት መለወጥና ማሻሻልም የለውጡ ሌላው አካል ነበር። አገልግሎቱ ከሞላ ጎደል በቴክኖሎጂ የተደገፈ እንዲሆን ጥረት ተደርጓል። የኢንቨስትመንት የሕግ ለውጥ መደረጉ የፈጠረው አንድ ትልቅ ለውጥ ቢኖር ቀደም ሲል ከውጭ አገር ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ ኢንቨስትመንቶች በተወሰኑ ዘርፎች ላይ ብቻ እንዲሰማሩ የሚያስገድድ ነበር። ይህን በአዋጅ 11/80/20/20 ላይ እንደተቀመጠው የውጭ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ ምቹ ሁኔታ የፈጠረ ነው። ኢትዮጵያ ከውስጥም ከውጭም የተፈጠረባት ጫና እና ኮቪድ ባይኖር ኖሮ አገራዊ ለውጡ ለኢንቨስትመንቱ የፈጠራቸው እድሎች ወደ ኢትዮጵያ የሚመጣውን ኢንቨስትመንት አሁን ካለው እንቅስቃሴ በላይ እንዲሆን ያስችል ነበር።

ለዚህም ነው ኮቪድም እያለና የሕልውና ዘመቻውም እየተካሄደ በ2013ዓ.ም ካለፉት አመታት በተሻለ በውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ውጤት ማስመዝገብ የተቻለው። የሕልውና ዘመቻውን ምክንያት በማድረግ ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ በኢትዮጵያ ላይ የኢኮኖሚ ጫና ለማሳደር አገሪቱ ላይ ፍጹም ሠላም እንደሌለ በማናፈስ ኢንቨስተሮች እንዲመጡ ለማድረግ ተሞክሯል።

በተለይም አሜሪካ ስታስጠነቅቅ ነበርና ይሄ የውጭ ኢንቨስተሮች እንዳይመጡ ያሳደረው ተጽእኖ ይኖር ይሆን? ስንል ለአቶ ተመስገን ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ፤ 2013 ዓ.ም ኢትዮጵያ የገባው የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ መጥቀስ ይቻላል። በበጀት አመቱ የተገኘው ገቢ የውጭ ኢንቨስተሮች እየመጡ መሆናቸውን ብቻ ሳይሆን በብዛት መምጣታቸውንም ጭምር የሚያሳይ ነው።

ከሶስት ነጥብ አንድ ቢሊየን ዶላር በላይ ኢንቨስትመንት መሳብ የተቻለው በዚህ ወቅት ነው። የ2014 ሩብ አመት አፈጻጸምም እንዲሁ ውጤታማ ነው። ብዛት ላላቸው ኢንቨስተሮች የንግድ ፈቃድ ተሰጥቷል።

በተጨማሪም ከእቅዱ 60 በመቶ በላይ ማሳካት ተችሏል። ይህ ኢትዮጵያ የሕልውና ዘመቻ ላይም ሆና በአምራችም፣ በግብርና ውጤቶች ማቀነባበርም ሆነ በአገልግሎት ዘርፍ ኢንቨስትመንቱ መቀጠሉን ያሳያል። አገራዊ ለውጥን ተከትሎ ከመጣ የሕግ ማሻሻል እርምጃ ያመጣው መሆኑ መዘንጋት የለበትም።

በችግር ውስጥ ውጤት ማስመዝገብ ከተቻለ አሁን ካለው በላይ በመሥራት የበለጠ ውጤት ለማምጣትም ሥራዎች ተገምግመው ክፍተቶችን እየለዩና ውጤታማ መሆኑን የማስቀጠሉ ተግባር ተጠናክሯል።

አዲስ ኢንቨስትመንቶችን ለመሳብ የምንቀሳቀሰውን ያህል ነባር ኢንቨስትመንቶችንም በማገዝ ረገድ በትኩረት መሥራት አለበት በሚል አዲስ ስትራቴጂ በመቅረጽ ወደ ተግባር ተገብቷል።በስትራቴጂው መሠረት ኢንቨስተሮች የሚያጋጧቸውን ችግሮች መፍታት፣ ያላቸውን ገንዘብም መልሰው ለኢንቨስትመንት እንዲያውሉ ሥራቸውን የሚያስፋፉበትን መንገድ በማገዝና ምቹ በማድረግ ረገድም ከ2013 ዓ.ም ጥር ወር ጀምሮ ኮሚሽኑ በስፋት እየሰራ ይገኛል። ኢንቨስትመንቱን እንዲህ የሚያነቃቁ ሥራዎችን በመሥራት ነው አገርን በኢኮኖሚ ወደላቀ ደረጃ ማሻገር የሚቻለው።

ከአገራዊ ለውጡ በፊት የነበረው የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ኢንቨስተሩን ተጠቃሚ በማድረግ ላይ ብቻ ያተኮረ እንደሆነ በስፋት ይነሳል። ይህም ከክትትልና ቁጥጥር ማነስና ተያያዥ የሆኑ ጉዳዮች ይነሳልና እዚህ ላይም ማብራሪያ እንዲሰጡ አቶ ተመስገን ለቀረበላቸው ጥያቄ «ኢንቨስትመንት እንደሚጀመረው ሁሉ የሚያልቅበትም ጊዜ አለ።ተፈጥሯዊ ሂደቱን ጠብቆ ነው የሚከናወነው። ኢንቨስትመንትን ስንስብ ታሳቢ የምናደርገው አራትና አምስት የሆኑ ዋና ዋና አላማዎች እንዲሳኩ ነው።

አንዱ የሚፈለገው ሀብት ወይንም ካፒታል ወደ አገር ውስጥ እንዲመጣ፣ ሌላው የመጣው ሀብት ሥራ ላይ ውሎ የሚፈለገውን የሥራ ዕድል እንዲፈጥር፣ ፕሮጀክቶች ወደ ሥራ ገብተው ዜጎች አስፈላጊውን የእውቀትና ቴክኖሎጂ ክህሎት እንዲያገኙ እና የሚፈለገው ቴክኖሎጂም አገር ውስጥ እንዲገባ፣ ሲሆን በአጠቃላይ ግን የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ከአገር ውስጥ ኢንቨስትመንት ጋር እንዲተሳሰር ማድረግ ነው።

በተለያየ ዘርፍ ላይ የተሰማሩት ኩባንያዎች ጥሬ እቃዎችን ከአገር ውስጥ እንዲጠቀሙ፣ ከአገር ውስጥ ተመሳሳይ ፕሮጀክቶች ጋርም በጥምረት እንዲሰሩ ማድረግ በመሆኑ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት በዚህ ውስጥ እንዲያልፍ ይጠበቃል። ከዚህ አንጻር ከዘርፍ ዘርፍ የተለያየ የሆነ ውጤት ነው የሚመዘገበው። አንዳንድ ዘርፎች ወቅታዊ የሆኑ ሥራዎችን ሰርተው ይወጣሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ ረጅም ጊዜ በመቆየት የኢትዮጵያ የልማት አጋር ሆነው ይሰራሉ።

ከዚህ አንጻር ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ቀጥተኛ የውጭ ኢንቨስትመንት ከስድስት ሺህ በላይ ሲሆን ሁሉም በሥራ ላይ ናቸው። በኮቪድና በተፈጠረው የፀጥታ ችግር ዘግተው የወጡ ኩባንያዎች በጣት የሚቆጠሩ ናቸው። ብዙዎቹ እንቅስቃሴያቸውን ለመቀጠል በጥረት ላይ የሚገኙ ናቸው» በማለት ምላሽ ሰጥተዋል።

ኢንቨስትመንቱን ምቹ ለማድረግ የሚያግዙ መሠረተ ልማቶችን ከማሟላት ጋር ያለውን እንቅስቃሴ አቶ ተመስገን እንደገለጹት፤ በአገር ደረጃ የተሠራው ለውጥ ኢትዮጵያ ለኢንቨስትመንት ምቹ እንድትሆን በመሆኑ የመንግሥት ድጋፍና ትኩረት ቀጣይነትን ያሳያል። ከመሠረተ ልማት መሟላትና ከፋይናንስ ድጋፍ ጋር የሚነሳውን ለመፍታትም በየጊዜው ማሻሻያዎች በማድረግ ለማገዝ ጥረት እየተደረገ ይገኛል። አሁን በስፋት እየተከናወነ ያለው የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴና ከየትኛው የዓለም ክፍል የሚመጡ የውጭ ኢንቨስተሮች እንደሆኑ ለቀረበላቸው ጥያቄም አቶ ተመስገን ምላሽ ሰጥተዋል። እርሳቸው እንዳሉት በአምራች ኢንደስትሪ ዘርፍ ላይ የሚሰማራው ከፍተኛውን ድርሻ ቢይዝም በአገልግሎት ዘርፍ ላይ የሚሰማሩ ኩባንያዎች ይገኛሉ።

ከኤሺያ፣ ከአውሮፓ፣ ከአረብ እና ከአፍሪካ አገሮች ከአሜሪካ የሚመጡ ናቸው። ኢትዮጵያ ከውስጥም ከውጭም የተከፈተባትን የኢኮኖሚ ጫና ለመቋቋም ብቸኛው አማራጭ በኢንቨስትመንት ዘርፍ ላይ ጠንክራ በመሥራት በመሆኑ በዚህ ረገድ ስላለው ቁርጠኝነትም አቶ ተመስገን «የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት በዋናነት በማደግ ላይ ባሉ አገራት የራሱ የሆነ የኢኮኖሚ አስተዋጽኦ አለው።

ኢትዮጵያ እየተከተለች ያለው የልማት አቅጣጫ የግሉን ዘርፍ ማበረታታትና መደገፍ ነው። የምናመጣቸው ኢንቨስትመንቶች በምንፈልጋቸው ዘርፎች ለምንፈልገው ዓላማ ግብ እንዲሆኑ በአግባቡ መከወናችንን ማረጋገጥ ይኖርብናል።

ከዚህ አንፃር የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን እንደ አንድ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት እንደሚያስተዳድር ተቋም ከማስተዋወቅ ጀምሮ ወደአገር የሚመጡ ኢንቨስትመንቶች ጥራታቸውን የጠበቁና ዘላቂ ጥቅም የሚያስገኙ ስለመሆናቸው በማረጋገጥ በአገር ደረጃም ኢንቨስትመንት የማሳደግ ጉዳይ ላይ ይሰራል። በተለይ ደግሞ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ከአገር ገጽታ ጋር ተያያዥ በመሆኑ በተቻለ ሥራዎች ይሰራሉ፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://www.press.et/ama/?p=61253

## ምርት ገበያው በአራት ወራት የ4 ነጥብ 4 ቢሊየን ብር ምርት አገበያየ

የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለፉት አራት ወራት 4 ነጥብ 4 ቢሊየን ብር የሚያወጣ የግብርና ምርት ማገበያየቱን ገለጸ።

ምርት ገበያው በተጠቀሰው ጊዜ 51 ሺህ 640 ሜትሪክ ቶን ቡና፣ ሰሊጥ፣ አኩሪ አተር፣ አረንጓዴ ማሾ፣ የተለያዩ የቦሎቄ ዝርያዎች እና አምስት ቶን የርግብ አተር አገበያይቷል።

የምርቶቹ መጠን 17 ሺህ 690 ቶን ቡና፣ 15 ሺህ 445 ቶን ሰሊጥ፣ 3 ሺህ 24 ቶን ነጭ ቦሎቄ፣ 4 ሺህ 731 ቶን አኩሪ አተር፣ 3 ሺህ 368 ቶን አረንጓዴ ማሾ፣ 1 ሺህ 904 ቶን ኸንጉርጉር ቦሎቄ፣ 215 ቶን ቀይ ቦሎቄና አምስት ቶን የርግብ አተር መሆናቸውን ምርት ገበያው ለኢዜአ የላከው መግለጫ አመላክቷል።

አረንጓዴ ማሾ በዓለም ገበያ ዋጋው እየጨመረ በመምጣቱ ምርት ገበያው የሚገበያይበት ዋጋም በከፍተኛ መጠን ጨምሯል።

በሐምሌ 2013 ዓ.ም 7 ሺህ 235 ብር የአንድ ኩንታል የአረንጓዴ ማሾ አማካይ የግብይት ዋጋ የነበረ ሲሆን በጥቅምት ወር ወደ 7 ሺህ 841 ብር አድጓል።

ይህ ዋጋ ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር በእጥፍ መጨመሩን መግለጫው ጠቁሟል።

የገበያው መጨመር አርሶ አደሮችና አቅራቢዎችን ተጠቃሚ እያደረገ መሆኑም ተገልጿል፤ በመጪው ወር ጥራት ያለው አረንጓዴ ማሾ በከፍተኛ መጠን ለገበያ እንደሚቀርብም ይጠበቃል።

በተመሳሳይ የቀይ ቦሎቄ ግብይት ከአምናው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር በመጠን ከ50 በመቶ በላይ፤ በዋጋ ደግሞ በእጥፍ ማደጉን ኢዜአ ዘግቧል፡፡

ይህ ለውጥ ሊመጣ የቻለው በግብይቱ ላይ ይስተዋል የነበረውን የኮንትሮባንድ እንቅስቃሴ በመግታትና የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ በመሰራቱ እንዲሁም የደንበኞችን ፍላጎት መሰረተ በማድረግ የአሰራር ማሻሻያ በመደረጉ እንደሆነ አመልክቷል።

ጥቁር አዝሙድ፣ ድንብላል፣ አብሽና ቁንዶ በርበሬ እንዲሁም ጓያ በዘመናዊ የግብይት ሥርዓቱ የተካተቱ ሲሆን ከተያዘው ምርት ዘመን አንስቶ ግብይት ይካሄድባቸዋል።

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://www.fanabc.com/ምርት-ገበያው-በአራት-ወራት-የ4-ነጥብ-4-ቢሊየ/

# የውጭ ምንዛሪ አጠቃቀምን የሚደነግግ አዲስ መመርያ ተዘጋጀ



የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የውጭ ምንዛሪ አጠቃቀምን በአግባቡ ለማካሄድ ያስችለናል ያለውንና አዳዲስ አሠራሮች የተካተቱበትን አዲስ መመርያ አወጣ፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ አዲስ ባወጣው የውጭ ምንዛሪ አጠቃቀም፣ ባንኮች የውጭ ምንዛሪ ሲፈቅዱ ቅድሚያ መስጠት ያለባቸው ለየትኞቹ ዘርፎች እንደሆነ በደረጃ በመከፋፈል ያስቀመጠበት ሲሆን፣ ከዚህ ቀደም ቅድሚያ ይሰጣቸው ያልነበሩ ምርቶች አሁን ቅድሚያ የሚሰጣቸው መሆኑን ያመላከተ ነው፡፡ ከዚህ ቀደም ከወጡ ተመሳሳይ መመርያዎች አንፃር ሲታይም አዳዲስ አሠራሮች የተካተቱበት ይህ መመርያ፣ የባንክ ቦርድ ዳይሬክተሮችና ሥራ አስፈጻሚዎች ይህንን መመርያ በማስፈጸም መሥራት አለባቸው ያላቸውን ዝርዝር ጉዳዮች ያስቀመጠ ነው፡፡

ባንኮች ካላቸው የውጭ ምንዛሪ ውስጥ 50 በመቶውን ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ዘርፎች መፍቀድ እንደሚኖርባቸው የሚጠቅሰው የመመርያው ክፍል፣ ከዚህ ቀደም ያልነበረ መሆኑንና በአዲሱ መመርያ እንዲካተት የተደረገ ነው፡፡ በአዲሱ መመርያ የተካተተው ሌላው አሠራር ደግሞ፣ ባንኮቹ ያልተጠቀሙበትን የውጭ ምንዛሪ ለብሔራዊ ባንክ ገቢ ማድረግ ያለባቸው መሆኑን መደንገጉ ነው፡፡ ከዚህም ሌላ የባንክ ሥራ አስፈጻሚዎች አስቸኳይ ለሚባል በተለይ እንደ መለዋወጫ ዕቃ ላሉ ምርቶች በቀጥታ የውጭ ምንዛሪ መፍቀድ የሚችሉ መሆኑ በመመርያው መቀመጡ አዲስ ነገር ነው፡፡ የብሔራዊ ባንክ የውጭ ምንዛሪ ሪዘርቭ አስተዳደር ዳይሬክተር የሆኑት የኔሐሳብ ታደሰ ለሪፖርተር እንደተናገሩት፣ አዲሱ መመርያ ለባንኮች እንቅፋት የሆኑ አሠራሮችን የሚያስወግድ ሲሆን፣ ቅድሚያ ላልነበራቸው ዘርፎች የውጭ ምንዛሪ የማግኘት ዕድል የሚሰጥ ነው፡፡ ቅድሚያ ሊሰጣቸው ይገባል ብሎ ካስቀመጣቸው ዘርፎች ውስጥ በመጀመርያው ረድፍ የተቀመጡት የፋርማሲውካል ግብዓቶችን፣ የምግብ ዘይት ግብዓቶችና ነዳጅን ነው፡፡ ይህም በተለይም በውጭ ምንዛሪ እጥረት ምክንያት ከአቅማቸው በታች ሲሠሩ ለነበሩ የዘይት ፋብሪካዎች ዕፎይታ ይሰጣል ተብሏል፡፡ የኢትዮጵያ የምግብ ዘይት አምራች ኢንዱስትሪዎች ማኅበር ዋና ሥራ አስኪያጅ አዲሴ ጋርኮቦ ለሪፖርተር እንደተናገሩት፣ የምግብ ዘይት ግብዓት በመጀመርያ ረድፍ መካተቱ ያለውን የዘይት እጥረት ይፈታል ብለዋል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ቅድሚያ ተሰጥቷቸው የውጭ ምንዛሪ ሊፈቀድላቸው ይገባል ተብሎ በመመርያው የተጠቀሱት ደግሞ የግብርና ግብዓቶች የሆኑትን ማዳበሪያ፣ ዘር፣ የአረም መድኃኒቶችና ኬሚካሎችን ነው፡፡

በሦስተኛ ደረጃ ላይ የተቀመጡት ወደ 15 የሚሆኑ ዘርፎች የተከፋፈሉ ምርቶች ሲሆን፣ ከእነዚህ ውስጥ በቀዳሚነት የውጭ ምንዛሪ ሊሰጣቸው ይገባል ተብሎ በመመርያው የተቀመጠው የሞተር ዘይት፣ የሞተር ቅባቶችና የግብርና የማሽነሪዎች ናቸው፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ከውጭ ምንዛሪ አጠቃቀም ጋር በተያያዘ ተደጋጋሚ መመርያዎችን የሚወጣ ሲሆን፣ በዚህ ሳምንት የወጣው አዲሱ መመርያ ለየት ብሎ የሚታይበት ከዚህ ቀደም በመጀመርያው ረድፍ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ተብሎ ከሚቀመጡት ውስጥ አንዱ የሆነውን ማዳበሪያ በዚህ መመርያ በሁለተኛው ደረጃ ቅድሚያ የሚሰጠው ተብሎ መቀመጡ ነው፡፡

ከዚህም ሌላ የምግብ ዘይት በአዲሱ መመርያ ከመጀመርያዎቹ ቅድሚያ ከሚሰጣቸው ምርቶች መካከል ተካትቶ የማያውቅ ቢሆንም፣ በአዲሱ መመርያ ከሦስቱ የውጭ ምንዛሪ ቅድሚያ ከሚሰጣቸው ምርቶች መካከል አንዱ ሆኗል፡፡

ይህ መመርያ ባንኮች የተሻሻለው ግልጽ የውጭ ምንዛሪ አጠቃቀምና አስተዳደር መመርያ፣ ብሔራዊ ባንክ ይህንን መመርያ የውጭ ምንዛሪ በጥንቃቄ ሊተዳደርና አዋጭ በሆነ መልኩ ጥቅም ላይ ሊውል የሚገባው ውስን ሀብት ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ግልጽና ተዓማኒ፣ አግባብነት ለጎደለውና ለኪራይ ሰብሰባቢዎች በር ከፋች ባልሆነ መንገድ ቅድሚያ ለሚሹና ለሌሎችም የኢኮኖሚ ወኪሎች መዋሉን ማረጋገጥ አስፈላጊ ስለሆነ እንዲህ ያለው መመርያ መውጣቱንም አመልክቷል፡፡

እያንዳንዱ ባንክ በውጭ ምንዛሪ ግብይት ላይ ተሳታፊ ስለሆነ፣ እያንዳንዱ ሠራተኛ ተጠያቂ ሊሆንበት የሚገባ ግልጽና ተዓማኒ የውጭ ምንዛሪ ግብይት አስተዳደር መመሪያና የአሠራር ሥርዓት ሊኖረው ስለሚገባ እንዲህ ዓይነት መመርያ መውጣቱን አመልክቷል፡፡

በዚህ መመርያ የባንኮችን ኃላፊነት በተመለከተ ከተቀመጡት ውስጥ በሌሎች የውጭ ምንዛሪ ግብይት ሕግጋት የተገለጹ ኃላፊነቶች የተጠበቁ ሆነው፣ የአንድ ባንክ ቦርድ የውጭ ምንዛሪ ግብይቶችን የተመለከቱ አጠቃላይ የውጭ ምንዛሪ ግብይት ሥራ አስተዳደራዊ መመርያዎችን በብሔራዊ ባንክ አዋጅ መሠረት የማዘጋጀትና በሥራ ላይ ማዋል እንደሚኖርበት ይደነግጋል፡፡ ከዚህም ሌላ የባንኩን አጠቃላይ ውጭ ምንዛሪ አቅርቦት በአስተማማኝ ደረጃ መያዙንና ካለው ሀብት ጋር የተዛመደ መሆኑን፣ ቢያንስ በየወሩ የመገምገም ኃላፊነት እንዳለባቸውም ያመለክታል፡፡ ይህንኑ ተግባር ለመመዘን ለመቆጣጠር በቂ የሆነ የሰው ሀብትና ቴክኒካዊ መዋቅር መኖሩን የማረጋገጥ፣ ቦርዱ ተግባራዊ ያደረጋቸው መመዘኛ መሥፈርቶች፣ አስተዳደራዊና የሪፖርት አቀራረብ ሥርዓቶች በአግባቡ መተግበራቸውንና የኃላፊነትና የሥልጣን ገደቦቻችን የተከተሉ መሆናቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት እንዳለበትም ያመለክታል፡፡ በተያያዘም የባንክ ሥራ አስፈጻሚዎች ተመሳሳይ ኃላፊነት የተሰጣቸው ሲሆን፣ በጣም የተለየ የውጭ ምንዛሪ ያስፈልጋቸዋል ለተባሉ ጥያቄዎች የውጭ ምንዛሪ እንዲፈቅዱ ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://ethiopianreporter.com/article/23953

# አዲሱ የውጭ ምንዛሪ አጠቃቀም መመርያና ክልከላዎች

የውጭ ምንዛሪ አጠቃቀምና አስተዳደርን በተመለከተ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ያወጣው አዲሱን መመርያ ባንኮች መተግበር ጀምረዋል፡፡ ይህ መመርያ በተለይ ከውጭ ምንዛሪ አፈቃቀድ ጋር በተያያዘ አዳዲስ አሠራሮችን የያዘም ነው፡፡ ባንኮች ከዚህ ቀደም ለደንበኞቻቸው ኤልሲ ሲከፍቱ ይተገብሯቸው የነበሩ አንዳንድ አሠራሮችን እንደሚከለክልና መመርያውን አለመተግበር የሚያስቀጣ እንደሆነም ያመላክታል፡፡

ከመመርያው መረዳት እንደተቻለው ከኤልሲ አፈቃቀድና አስተዳደር ጋር በተያያዘ «ክልከላ» በሚል ራሱን በቻለ አንቀጽ ያስቀመጠው ድንጋጌ፣ ከዚህ ቀደም ይሠራባቸው የነበሩ አንዳንድ አሠራሮች ተፈጻሚ የማይሆኑ መሆኑን የሚያመለክትባቸው ናቸው፡፡ በዚሁ መሠረት በዚህ መመርያ በዋናነት ክልክል ተግባራት ናቸው ብሎ ካስቀመጣቸው መካከል በልዩ ሁኔታ ከሚፈቀደው ውጪ ማንኛውም ባንክ በምንም ሁኔታ ከኤክስፖርት የተሰባሰበ የውጭ ምንዛሪን ለገቢ ንግድ ሥራ ማዋል የማይቻል መሆኑን የሚደነግገው ክፍል አንዱ ነው፡፡ በዚህ በመመርያ የተከለከለ ተግባር መሆኑን ያስቀመጠው ጉዳይ ደግሞ የግዥ ትዕዛዞችን ለመፍቀድ ደንበኛው ሙሉ በሙሉ የሚፈለግበትን የገንዘብ መጠን ገቢ ከማድረግ ጋር ይያያዛል፡፡ ይህንንም «በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ግልጋሎት ላይ የሚውል ካልሆነ በስተቀር፣ ማንኛውም ባንክ ሙሉ የገንዘብ መጠኑን ገቢ ሳያደርግ የሲኤዲ (ካሽ አጌንስት ዶክመንት) ግዥ ትዕዛዞችን መፍቀድ አይችልም» በሚል አስቀምጦታል፡፡

ከእነዚህ ሁለት ክልከላዎች ባሻገር ማንኛውም ባንክ ቢያንስ ሰላሳ በመቶውን የኤልሲ (ሌተር ኦፍ ክሬዲት) መጠን በቅድሚያ በጥሬ ገንዘብ ገቢ ሳይደረግ፣ የሌተር ኦፍ ክሬዲት (ኤልሲ) ማምልከቻዎችን መፍቀድ የማይችል መሆኑንም መመርያው አመልክቷል፡፡ ሆኖም የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ የወጪ ንግድን ከዚህ ገደብ ነፃ ማድረግ የሚቻል መሆኑን ጠቁሟል፡፡

በዚህ መመርያ እንደ አዲስ አሠራር ተደርጎ የተቀመጠውና ክልከላ በሚለው አንቀጽ ውስጥ የተቀመጠው ድንጋጌ፣ በዓለም አቀፍ የክፍያዎች አፈጻጸም ልምድ መሠረት ለአቅራቢ ክፍያ ሳይፈጸም ማንኛውም ባንክ የሲኤዲ ሰነዶችን ለደንበኞቻቸው መስጠት የሌለባቸው መሆኑን ነው፡፡ ይህንኑ ድንጋጌ በማመሳከርም የውጭ ምንዛሪን መተላለፍን ለማረጋገጥ በሦስት ቀናት ውስጥ የተጠቃሚነት ደረሰኝ (ዩቲላይዜሽን ቲኬት) መዘጋጀት እንዳለበት አመልክቷል፡፡ ሌላው ክልከላን የተመለከተው ድንጋጌ፣ ማንኛውም ባንክ ጊዜው ያለፈበት ኤልሲና የግዥ ትዕዛዝ ሳይፀድቅ ለተጫኑ ዕቃዎች ፈቃድ መስጠት የማይችል መሆኑን ስለመሆኑ ማመላከቱ ነው፡፡ ሆኖም ዕቃዎቹ ከመጫናቸው አስቀድሞ የሚቀርብ አሳማኝ የኤልሲና የግዥ ትዕዛዝ አገልግሎት ጊዜ ማራዘሚያ ተቀባይነት እንደሚኖረው ይጠቅሳል፡፡ ኤልሲ ወይም ግዥ ትዕዛዝ ከመፅደቁ አስቀድሞ ለተጫኑ ዕቃዎች፣ ለአስመጪ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት የአስመጪ ፈቃድ እንዲሰጥ ማፅደቅ የሚቻል መሆኑንም ይኼው መመርያ ያመለክታል፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ያወጣው መመርያ የውጭ ምንዛሪ አመዳደብና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ዘርፎች በተመለከተ፣ እንዲሁም ባንኮች የውጭ ምንዛሪ ምደባን በሚመለከት ማድረግ ያለባቸውን አሠራር በዝርዝር ያስቀመጠ ሲሆን፣ ከዚህ በኋላ የውጭ ምንዛሪ አፈቃቀድ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ዘርፎች በየደረጃው በማስቀመጥ የሚሠራበት ነው፡፡ ይህንንም ደረጃ መመርያው በሦስት ዋና ዋና ዘርፎች በመከፋፈል አስቀምጦታል፡፡ የውጭ ምንዛሪ ምደባን በሚመለከት ባንኩ በቀጣይ አንደኛ የመጀመርያ ደረጃ ቅድሚያ፣ ሁለተኛ ተከላካይ ደረጃ ቀዳሚና ቀጣይ፣ ሦስተኛ ደረጃ ቅድሚያ የገቢ ንግድ ዕቃ ዓይነቶች መደብና ክፍያዎች መሠረት እንደ ቅደም ተከተላቸው ወረፋቸው ቅድሚያ የሚሰጣቸው ይሆናል፡፡ በመመርያው መሠረት የመጀመርያ ወይም በአንደኛ ደረጃ ቅድሚያ የውጭ ምንዛሪ የሚፈቀድላቸው ዘርፎች ተብለው የተጠቀሱት በፋርማሲዩቲካልስ ዘርፍ ሥር የተዘረዘሩት መድኃኒቶች፣ የመድኃኒት ማምረቻዎች፣ አምራቾች፣ ግብዓቶችና የቤት ሙከራ ውሁዶች፣ የላቦራቶሪ ኬሚካሎች፣ የምግብ ዘይት ማምረቻዎች፣ ግብዓትና ፈሳሽ ፔትሮሊየም ጋዝ ናቸው፡፡

በሁለተኛው ደረጃ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ዘርፎች ተባለው የተጠቀሱት ደግሞ የግብርና ግብዓቶች መዳበሪያ፣ ዘር፣ ፀረ አረምና ኬሚካል፣ የማኑፋክቸሪንግ ግብዓቶች፣ የምርት ጥሬ ዕቃዎችና ኬሚካሎች ናቸው፡፡ መመርያው በሦስተኛ ደረጃ ያስቀመጣቸው ምርቶች ደግሞ በርካታ ሲሆኑ፣ ከእነዚህ ውስጥ በቀዳሚነት የተቀመጡት የሞተር ዘይት፣ ቅባቶች፣ የግብርና ግብዓቶችና ማሽነሪዎች ናቸው፡፡ የግብርና ግብዓቶችና ማሽኖች ሥር የመስኖ ውኃ ፓምፖች፣ የእንስሳት መኖዎች፣ ማሽነሪዎችና መሣሪያዎች፣ ትራክተሮች፣ መዝሪያ ማሽነሪዎችና የመለዋወጫ ዕቃዎች ሲሆኑ፣ በሦስተኛ ደረጃ ውስጥ የተቀመጡት ሌሎች ምርቶች ደግሞ ፋርማሲዩቲካል ምርቶች ሲሆኑ፣ እነሱም የላቦራቶሪ መሣሪያዎች፣ የሕክምና መሣሪያዎችና መገልገያዎች፣ የአምራች ኢንዱስትሪዎች፣ የማሽነሪ ማምረቻ ማሽኖች መሣሪያዎች፣ መለዋወጫዎችና ተጓዳኝ ዕቃዎችና የግዥ ጥያቄዎች መሆናቸውን ያመለክታል፡፡ በንጥረ ምግብ የበለፀጉ የሕፃናት ምግቦች በሦስተኛ ደረጃ ቅድሚያ የሚሰጠው ነው፡፡ መጠናቸው ከ50,000 ዶላር ያልበለጠ የኮንስትራክሽን ድርጅቶች ለራሳቸው ማሽነሪዎችና መሣሪያዎች መለዋወጫ መሣሪያዎች የሚያስፈልገው የውጭ ምንዛሪ፣ እንዲሁም የመማሪያ ደብተሮች፣ እስክርቢቶዎች፣ እርሳስሶችና የኅትመት ወረቀቶችም በዚሁ ምድብ ሥር ናቸው፡፡

መመርያው የውጭ ምንዛሪ የሚጠይቁ የትርፍ ክፍፍል ክፍያንም በዚሁ ምድብ ያስቀመጠ ሲሆን፣ በመመርያው የንግድ ሥራ ትርፍና የትርፍ ክፍፍል (ዲቪደንድ) ገንዘብ ዝውውር፣ በሚል ተገልጿል፡፡ የውጭ አገር አየር መንገዶች ተጨማሪ ሽያጭ ገንዘብ ዝውውር የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ድርጅቶች የአክሲዮን ድርሻ ሽያጭም በሦስተኛው ምድብ ሥር ናቸው፡፡ እንዲህ ባለው መልክ የተቀመጠው የውጭ ምንዛሪ፣ አጠቃቀምና ለዚህ የገቢ ንግድ ዕቃዎች በባንክ የሚመደበው የውጭ ምንዛሪ መጠን በማንኛውም ጊዜ ለምርትና አገልግሎቶች ገቢ ንግድ ከሚመደበው አጠቃላይ የውጭ ምንዛሪ መጠን ከሃምሳ በመቶ ያነሰ መሆን እንደማይገባውም በመመርያው ተደንግጓል፡፡ ይኼው የተመደበው ሃምሳ በመቶ የውጭ ምንዛሪ ውስጥ አሥራ አምስት በመቶ ለመጀመርያው አንደኛ ደረጃ ቀዳሚዎች፣ አርባ አምስት በመቶው በሁለተኛ ደረጃ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ምርቶች፣ እንዲሁም አርባ በመቶው ለቀጣይ ሦስተኛ ደረጃ ቀዳሚዎች የሚከፋፈል መሆኑን መመርያው ያመለክታል፡፡

የገቢ ንግድ ዕቃዎች የተመደበው በማንኛውም ጊዜ ለገቢ ምርትና አገልግሎት ከሚመደበው አጠቃላይ መጠን ሃምሳ በመቶ የማያንስ ሆኖ ቢገኝ ግን፣ በቀጣዩ ወር አምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ባንኩ ልዩነቱን ለብሔራዊ ባንክ ፈሰስ እንዲያደርግ ማድረግ ግዴታ መሆኑን ይኼው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመርያ ያመለክታል፡፡

ከዚህም ሌላ ከተመደበው የውጭ ምንዛሪ ጥቅም ላይ የዋለው መጠን በማንኛውም ጊዜ ለገቢ ምርትና አገልግሎቶች የዋለው መጠን በማንኛውም ጊዜ ለገቢ ምርትና አገልግሎቶች የጠቅላላ መጠን ከሃምሳ በመቶ ያነሰ ሆኖ ቢገኝ፣ ልዩነቱን በየስድስት ወራት ባንኮቹ ለብሔራዊ ባንክ ፈሰስ እንዲያደርጉ ያስገድዳል፡፡ ይህንን ፈሰስ የተደረገ ገንዘብ ብሔራዊ ባንክ በወቅቱ አማካይ የምንዛሪ ተመን ተመጣጣኝ የብር መጠን ክፍያውን ወደ ባንኩ ተቀማጭ ሒሳብ ገቢ የሚያደርገው መሆኑንም በመመርያው ተጠቅሷል፡፡

በዚህ መመርያ ውስጥ የተከለከለው ከተቀመጡ አንቀጾች ውስጥ የባንክ ሥራ አስፈጻሚዎች በተለየ ውሳኔ ሊሰጡባቸው ይችላሉ የተባሉ ጉዳዮች መጠቀሳቸው ነው፡፡ ለአብነትም ያህል በማምረቻ ማሽነሪዎች አካላት ወይም መሣሪያዎች አካላት ላይ በተከሰተ ጉዳት፣ እንዲሁም አነስተኛ የገንዘብ መጠን ባላቸው ወሳኝ ግብዓቶች ምክንያት የምርት መስተጓጉል እንዳይፈጠር፣ የባንኩ ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚ (ቺፍ ኤግዚኪዩቲቭ ኦፊሰር) ከማኑፋክቸሪንግ ወይም ከግብርና መስክ የሚቀርቡ የመለዋወጫ መሣሪያዎች ከውጭ የማስገባት ጥያቄ የመፍቀድ ሥልጣን የተሰጠው መሆኑ ይጠቀሳል፡፡

በብሔራዊ ባንክ የገንዘብ (ሞኒተሪ) ዘርፍ ገዥ ወይም ምክትል ገዥ ለፋይናንስ ተቋማት፣ ለፌዴራል መንግሥትና የክልል መንግሥት፣ እንዲሁም የከተማ አስተዳደሮችን ጥያቄዎች እንደተናጠል ጉዳዮቻቸው ልዩ ቅድሚያ ፈቃድ ሊሰጥ እንደሚችልም ይህ መመርያ ይደነግጋል፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ፣ የባንክ የቦርድ አመራሮችና ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች በዚህ መመርያ መሠረት በየደረጃቸው ተጠያቂ የሚሆኑበትን አሠራር ያመለካተ ሲሆን፣ የውስጥ ኦዲተርም የራሱ ኃላፊነት ተሰጥቶቷል፡፡ የየባንኩ የውስጥ ቁጥጥር ኦዲት ሥራ ቢያንስ በስድስት ወራት አንድ ጊዜ እንደ አስፈላጊነቱ ድንገተኛ ፍሻዎችን በማድረግ፣ የውጭ ምንዛሪ ግብይት ሥራዎች ከመመርያዎች ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡

የኦዲት ግኝቶቹም ለሚመለከተው የባንኩ አመራር ቦርድ፣ እንዲሁም የበላይ ኃላፊዎች መቅረብ ያለበት ሲሆን፣ የውስጥ ኦዲት ሪፖርት ቅንጅትም ለአመራር ቦርዱ በቀረበበት ተመሳሳይ ጊዜ በብሔራዊ ባንክ ለውጭ ምንዛሪ ግብይትና ተቀማጭ አስተዳደር መላክ እንደሚኖርበት ያመለክታል፡፡

በዚህ መመርያ የቀረበውን የትኛውንም መሥፈርት በምንም ዓይነት መልኩ የተላለፈ ማንኛውም ባንክ፣ በእያንዳንዱ መመርያ የሕግ ጥሰቱ አምስት ሺሕ ዶላር ቅጣት የሚቀጣ ስለመሆኑ ተጠቅሷል፡፡

ከዚህ ቅጣት ሌላ ይህንን መመርያ በሚፃረር መልኩ ማንኛውም ባንክ በመመርያው የተገለጹትን ሁሉ ተግባራዊ ያላደረገ ወይም በሌላ በምንም ዓይነት መልኩ ተነሳስቶ መመርያውን የተላለፈ ወይም ተግባራዊነቱንም ያስተጓጎለም በብሔራዊ ባንክ መቋቋሚያ አዋጅ መሠረት ተጠያቂ እንደሚሆንም አመልክቷል፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://ethiopianreporter.com/index.php/article/24005

# ከኢትዮጵያ ጎን የቆሙ አጋር አገሮች ኢኮኖሚያዊ ድጋፍ

አሸባሪው ሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ ቡድን አሁንም መሸቶበት እንኳን ያልሞት ባይ ተጋዳይነቱን ቀጥሎበታል፡፡ በሰላም እጅ እንዲሰጥ ከኢትዮጵያ መንግሥት ጥሪ ቢቀርብለትም ፈቃደኝነቱን ከማሳየት ይልቅ ጉድጓዱን አርቆ መቆፈር መርጧል፡፡ ቡድኑ እንዳሰበው ተሳክቶለት ቢሆን ኢትዮጵያ ዛሬ ፈራርሳ በታየች ነበር፡፡

በአንድነቱ የሚያምን ጽናት ያለው፣ ሰላም ወዳድ ህዝብ ያላት አገር መቼም እንደማትወድቅና እንደማትፈርስ አሸባሪውም ሆነ ዜጎቻቸው ከኢትዮጵያ እንዲወጡ ሲወተውቱ የነበሩትም ሀቁን ላለመቀበል እንጂ ልባቸው ጠንቅቆ ያውቀዋል፡፡

አሜሪካና አንዳንድ የአውሮፓ አገራት ዜጎቻቸው ከኢትዮጵያ ለቀው እንዲወጡ ወትውተዋል። ወደ ኢትዮጵያ ዝር የሚል ዓለምአቀፍ ማህበረሰብ እንዳይኖር ጭምር ነበር ማስጠንቀቂያቸው፡፡ ጦርነቱ ከሚካሄድበት አካባቢ አልፎ አዲስ አበባ ከተማም የጦርነት አውድማ እንደምትሆን ዓይነት ነበር የዜጎች ለቃችሁ ውጡ ዘመቻው፡፡ ኢትዮጵያ ጦርነቱ ሲበረታባትና ኢኮኖሚያዋም ሲዳከም እጅ ትሰጣለች ነበር እሳቤው። ግን ያለሙት አልሆነም፡፡

ኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳዩዋን በራሷ መፍታትና መፍትሔ እንዳትሰጥ ጣልቃ በመግባት ብዙ ጥረት አድርገዋል ወጥተው ወርደው ሠርተዋል በማስፈራሪያ ጭምር ሽብር ሲነዙ ከርመዋል። መንግሥት ያሳየውን ትዕግስት ከሽንፈት በመቁጠር ብዙ ዕርምጃ ተጉዘዋል፡፡ ጦርነቱ እንዲባባስ አንዴ በሰብዓዊ ድጋፍ፣ ሌላጊዜ ደግሞ የተኩስ አቁም ስምምነት እንዲደረግ፣የሽግግር መንግሥት እንዲቋቋም ብቻ ከሽብርተኛው ጎን ሆነው ያልሸረቡት ነገር የለም፡፡

ግን ሁሉም እንቅስቃሴያቸው ከሽፎባቸዋል፡፡ በተለይም ዜጎቻቸው ከኢትዮጵያ እንዲወጡ ይደረግ የነበረው ውትወታ በመአድን ልማት፣ በግብርና ውጤቶች ማቀነባበር፣ የንግድና አገልግሎት ዘርፎች ላይ የተሰማሩ የተለያዩ የውጭ ኩባንያዎችም ከኢትዮጵያ እንዲወጡ የሚገፋፋ ጭምር ነው አካሄዳቸው፡፡ ግን ደግሞ ሀብቱን ያፈሰሰበትንና ትርፍ ያገኘበትን ለቆ ለመውጣት የሞከረም ብዙ የውጭ ኩባንያ አልታየም፡፡

ይልቁንም አጠናክሮ ለመቀጠል ቃል የገባና ሥራ ለመጀመር ፍላጎት ያላቸው ኩባንያዎች መኖራቸው ነው እየታየ ያለው፡፡ ከኢትዮጵያ ጎን የቆሙ ወዳጅ ሀገራት አጋርነታቸውን በማሳየት አሳፍረዋቸዋል፡፡

ከወዳጅ ሀገራት መካከልም በማአድን ዘርፉ ተሰማርተው በኢትዮጵያ በመንቀሳቀስ ላይ ከሚገኙ ሀገራት የእስራኤል የማእድን ኩባንያ ይጠቀሳል፡፡ ይኸው ዋና መስሪያ ቤቱን በእስራኤል ያደረገው ሌካ የተባለውና በማዕድን ዘርፍ የተሰማራው ኩባንያ የሥራ ኃላፊዎች ሰሞኑን ከማዕድን ሚኒስትር ኢንጂነር ታከለ ኡማ ጋር በሚኒስቴሩ መስሪያ ቤት ተገኝተው ምክክር ባደረጉበት ወቅት ኩባንያው ሥራውን አጠናክሮ እንደሚቀጥል ማረጋገጡን ከሚኒስቴሩ ማህበራዊ ድረገጽ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡

በምክክሩ ወቅትም ሚኒስትሩ ኢንጂነር ታከለ ኡማ «በክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ አመራር መንግሥት ብልጽግናን በሀገራችን ለማስፈን የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ማሻሻያ ዕርምጃዎችን በቁርጠኝነት ሲወስድ ቆይቷል፡፡

አገራችን በፈተና ላይ በምትገኝበት በዚህ ወቅት በግሉ ዘርፍ ኢንቨስትመንት ከፍተኛ ፋይዳ አለው፡፡ የእስራኤል የማዕድን ኩባንያዎች በዚህ ወሳኝ ወቅት ከኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ጎን ለእውነት ወግናችሁ ስለቆማችሁ ምስጋና ይገባቸኋል» ሲሉ ተናግረዋል፡፡ በምክክሩ ላይ የተገኙት በእስራኤል የኢትዮጵያ አምባሳደር ረታ ዓለሙ በበኩላቸው፤ በኢትዮጵያ በማእድን ልማት ላይ የተሰማሩ የእስራኤል ማዕድን

ኩባንያዎች ተወካዮች በዘርፉ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ አበረታች መሆኑን እንዲሁም የኩባንያዎቹ ኃላፊዎች በዚህ ወሳኝ ወቅት ከኢትዮጵያ ጎን እንደሚቆሙና ሥራቸውንም አጠናክረው እንደሚቀጥሉ ማረጋገ ጣቸውን የሚኒስቴሩ መረጃ ያመለክታል፡፡ አምባሳደር ረታ ኢትዮጵያ እና እስራኤል ጠንካራ ታሪካዊ እና መንፈሳዊ ትስስር ያላቸው መሆኑን በማስታወስ፣ የግሉ ዘርፍ ኢንቨስትመንት በሁለቱ አገራት መካከል ያለውን ወዳጅነት ለማጠናከር ትልቅ አስተዋፅኦ ማበርከት እንደሚችል ነው የተናገሩት፡፡

በዚሁ ወቅት የማዕድን ሚኒስቴር እና ተጠሪ ተቋማት ሠራተኞች በወቅታዊና አገራዊ ጉዳይ ላይ ባደረጉት ውይይት ወቅቱ ትብብርን የሚጠይቅ እንደሆነና ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ሀገርን የማስቀጠል ዘመቻውን በመደገፍ ሀገራዊ ግዴታውን መወጣት እንዳለበት መግለጻቸውን መረጃው አስታውሷል፡፡

ኢትዮጵያ ካለችበት ሁኔታና ኢኮኖሚዋን ከሚያዳክም ጫና እንድትወጣ ከመንግሥት ብቻ ሳይሆን፣ የዜጎቿና የወዳጆቿም ያላሰለሰ የጋራ ጥረት እንደሚጠይቅ ነው በሚኒስቴሩ ከተካሄደው ውይይት መረዳት የሚቻለው፡፡ በኢትዮጵያ የሚገኙ በተለያየ ዘርፍ ላይ የተሰማሩ ኩባንያዎች ሥራቸውን እንዲቀጥሉና ዜጎቸዋም ተረጋግተው እንዲኖሩ በኢትዮጵያ ላይ እምነቷን የጣለችው ቻይናም አጋርነቷን አሳይታለች፡፡ በተግባር የተደገፈ ድጋፏንም አረጋግጣለች፡፡

ረቡዕ እለት አዲስ አበባ ከተማ የገቡት የቻይና ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዋንግ ዪ ኢትዮጵያ የውጭ ጣልቃገብነት ሳያስፈልጋት የራሷን ጉዳይ በራሷ መፍታት እንዳለባትም ተናግረዋል። በሴኔጋል በሚካሄደው ስምንተኛው የቻይና-አፍሪካ የሚኒስትሮች ምክርቤት ጉባኤ በሴኔጋል ዳካር ላይ ቻይና ለአፍሪካ የግብርና ምርቶች ከቀረጥ(ታሪፍ)ነፃ የገበያ ዕድል ለመስጠት መወሰኗንም አስታውቃለች፡፡

ቻይና የፈጠረችውን መልካም ዕድል፣ የማእድን ሀብቱን አሁን ካለው የኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ጋር አያይዘው የምጣኔ ሀብትና የፖሊሲ ባለሙያው ዶክተር ቆስጠንጢኖስ በረኸተስፋ በሰጡት ትንታኔ፤ ኢትዮጵያ ባላት የመሬት ስፋትና የማእድን እምቅ ሀብት፣ የተማረና ጉልበት ያለው የሰው ኃይል ብዙ መሥራትና ውጤታማ መሆን እንደሚቻል ያምናሉ። ኢትዮጵያ ጫና ውስጥ ሳትገባ ለኢኮኖሚ ትልቅ አውታር የሆኑ ሀብቶቿን የምትጠቀምበት ዕድል ያላት ሀገር ናት፡፡ ይሁን እንጂ እስከአሁን የወጪ ንግዷ በስፋት ትኩረት ያደረገው በቡና እና የቅባት እህሎች ላይ ነው፡፡

የማእድን ሀብቷ ግን ከእነዚህ ምርቶች ባልተናነሰ ገቢ የሚያስገኝ መሆኑ መታወቅ ይኖርበታል፡፡ ከእነዚህ መካከል አንዱ ነዳጅ ሲሆን፣ የወርቅና ሌሎች የመአድን ሀብቶችም ተጨማሪ ናቸው፡፡ በተለይም ኢትዮጵያ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ወጪ ከምታወጣባቸው ዘርፎች አንዱ ነዳጅ በመሆኑ እዚህ ላይ ትኩረት ተሰጥቶ ቢሠራና ከዚህ ቀደም በዘርፉ የተጀመሩ ሥራዎች ቢጠናከሩ ብዙ ማትረፍ ይቻላል፡፡ በመሆኑም ማእድን ፍለጋ የሚመጡ ኢንቨስተሮች ፍላጎታቸው ምን እንደሆነ፣ የመንግሥት የቁጥጥር ስልት ተለይቶና ታስቦበት ቢሠራ የተሻለ ይሆናል፡፡

ለአብነት ኢትዮጵያ ያላትን የነዳጅ ሀብት በቦታው ላይ ወደ ናፍጣና ወደ አውሮፕላን ነዳጅ መቀየር የሚቻልበት ቴክኖሎጂ ስላለ መጠቀም ይቻላል፡፡ እነዚህ ሀብቶች በሰላሙም ጊዜ ቢሆን በከፍተኛ ደረጃ የሚያስፈልጉ ናቸው፡፡ ማእድን በርከት ያለ መዋእለነዋይ ሊገኝበት የሚችል ሀብት ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜም ነዳጅ፣ ወርቅ፣ አልማዝ፣ መዳብ በመሸጥ እየተጠቀሙ ያሉ ሀገራት በከፍተኛ ሀብት ላይ ነው የሚገኙት፡፡ ኢትዮጵያም ሀብቱ ስላላት ጥቅም ላይ በማዋል ከውጭ ምንዛሪ ጫና እንድትላቀቅ ያስፈልጋል፡፡

ይህ ሲሆን በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ወደ አገር ውስጥ የሚገባውን ምርት ማስቀረት ይቻላል፡፡ እንደ ዶክተር ቆስጠንጢኖስ ገለጻ፤ ጊዜው አሁን አፋጣኝ የሆነ ውሳኔ የሚሰጥበት ወቅት ነው፡፡ ምክንያቱም ሀገሪቱ በአንድ በኩል ህዝቧን መንከባከብ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በተለያየ መንገድ ለጦርነቱ የሚወጣውን ወጪ መተካት ይኖርበታል፡፡ ይህ ደግሞ በመንግሥት ላይ የሚጣል ብቻ መሆን የለበትም፡፡ ከተለያዩ አካላት ተሳትፎ ይጠበቃል፡፡ ሀገሪቱ ውስጥ የሚገኙት ከ50 በላይ የሚሆኑ ዩኒቨርሲቲዎች፣ በተለይም የፖሊሲ፣ የጂኦሎጂና ኢንቨስትመንት ጥናት የሚያካሂዱ በዚህ ወቅት ይፈለጋሉ፡፡ ሰፋ ያለ ውይይትና ምክክር ሲኖር መፍትሔና ውጤት ይገኛል። እንደነ አሜሪካ፣ሩሲያ፣አውሮፓ ህብረት፣ ጃፓን፣

ቻይና ያሉ አገራት ቲንክታንክስ የሚባሉ ሃሳብና ትችት የሚያቀርቡ የምርምር ተቋማት አሏቸው። ኢትዮጵያም እንደአስፈላጊነቱ እንዲህ ያለውን አሠራር በመከተል ጉዳዩ ሰፋ ባለ መልኩ እንዲታይና በመንግሥት ላይ ብቻ ተንጠልጥሎ እንዳይቀር ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በዓለምአቀፉ በኩል ኢትዮጵያን በኢኮኖሚ ለማዳከም እየተደረገ ስላለው ጫና በተመለከተም ዶክተር ቆስጠንጢኖስ በሰጡት ትንታኔ የሚያስፈራ ወይንም የሚያሰጋ ነገር የለም፡፡ አሜሪካ ኢትዮጵያ ከነፃ ገበያ ዕድል (ከአገዋ) እንድትወጣ በመሪዋ በኩል የተላለፈው ገና ውሳኔ አላገኘም፡፡ ጉዳዩ ለአሜሪካን ተወካዮች ምክርቤት ቀርቦ ለውሳኔ እተጠበቀ ነው። ውሳኔው ወይ ይወድቃል ወይንም ይፀድቃል፡፡

በመሆኑም ከወዲሁ ተስፋ መቁረጥ አያስፈልግም፡፡ አፍሪካ ፍሪ ኮንቲነንታል ትሬድ ኤሪያ የሚባል ኢትዮጵያ መፈረሟ መዘንጋት የለበትም። ይህ የፊርማ ስምምነት ምርቶቻቸውን ያለቀረጥ ክፍያ ወደ ሌሎች አፍሪካ አገሮች መላክ የሚያስችል ዕድል ነው፡፡ በሁለተኛ ደረጃ መታየት ያለበት ደግሞ በአሁኑ ጊዜ በአገዋ ዕድል ተጠቅመው ምርቶቻቸውን ወደ አሜሪካን ሀገር በመላክ ይጠቀሙ የነበሩ እንደነ ባንግላዴሽ፣ ቬትናም ያሉ ሀገሮች በኮቪድ 19 ቫይረስ ወረርሽኝ ቀውስ ምክንያት የሚልኩት የምርት መጠን እየቀነሰ ነው፡፡ ሀገራቱ የሚልኩት ምርት መቀነሱ ለኢትጵያ የገበያውን ዕድል ያሰፋላታል፡፡

በመሆኑም የኢትዮጵያ አምራቾች፣ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ዕድሉን መጠቀም ይችላሉ፡፡ በተጨማሪ ደግሞ የኢትዮጵያ ዲፕሎማቶችም የሚጠበቅባቸውን የዲፕሎማሲ ሥራቸውን በአግባቡ መወጣት ከቻሉ በተለያየ መንገድ እየተፈጠረ ያለው የኢኮኖሚ ጫና ስጋት ከንቱ ይሆናል፡፡ ከወደቻይና የተሰማው መልካም ብስራት ደግሞ ኢኮኖሚው እንዲያንሰራራ የሚያደርግ ነው።

በሴኔጋል በሚካሄደው ስምንተኛው የቻይና-አፍሪካ የሚኒስትሮች ምክርቤት ጉባኤ በሴኔጋል ዳካር ላይ ቻይና ለአፍሪካ የግብርና ምርቶች ከቀረጥ (ታሪፍ) ነፃ የገበያ ዕድል ለመስጠት መወሰኗን ነው፡፡ በገንዘብ ሲተመንም ከአፍሪካ በሚቀጥሉት ሦስት ዓመታት ወደ አገሪቱ የሚላከው ምርትም ወደ ሦስት መቶ ቢሊየን ዶላር ይገመታል፡፡ ቻይና የፈጠረችው ዕድል አገዋን ሊተካ የሚችል ትልቅ ትርጉም ያለው ነገር ነው። ከዚህ በኋላ እንደሀገር በትኩረት መሠራት ያለበት ኢንዱስትሪዎች በጥራትና በስፋት እንዲያመርቱ ማስቻልና ደንበኛ ተኮር ምርት እንዲያመርቱ ማድረግ ነው፡፡

ዶክተር ቆስጠንጢኖስ እንዳሉት፤ በዓለምአቀፉ ከሰብዓዊ መብት ጋር ተያይዞ የሚነገረው ደግሞ በሂደት በዲፕሎማሲ የሚፈታ ጉዳይ ነው፡፡ በደፈናው የምዕራቡ የመገናኛ ብዙሃን እና አንዳንድ የመንግሥት ተወካዮች መግለጫ በሰጡ ቁጥር መደናገጥ ተገቢነት የሌለው ስጋት ነው፡፡ እውነቱን ይዞ እስኪገባቸው ማስረዳት ግን ይጠበቃል፡፡ አንረዳም ብለው ጽንፍ ከያዙ ደግሞ ጊዜ እየፈታው የሚሄድ ይሆናል፡፡

ትኩረቱ መሆን ያለበት ኢትዮጵያ ከገባችበት የተለያየ ጫና እንዴት መወጣት አለባት፣ በጫና ውስጥ ሆኖ የልማቱ ሥራ እንዴት መከናወን እንዳለበት፣ የወጪ ንግዱ ስለሚጠናከርበት፣ በጦርነት የተጎዱ ወገኖችን መልሶ ስለማቋቋም ብቻ ነው ማሰብ የሚፈለገው፡፡ ጦርነቱ ሲያበቃ ደግሞ የዓለምአቀፉ ማህበረሰብ በራሱ በሰብዓዊ ዕርዳታና መልሶ በማቋቋም መሳተፋቸው አይቀርም፡፡ አሜሪካን ደግሞ ከኢትዮጵያ ጋር በዲፕሎማሲና በተለያየ መንገድ ግንኙነት ያላት ሀገር ናት፡፡

ኢትዮጵያ በየጊዜው በውስጥም በውጭም ፈተናዎች ቢገጥሟትም እንደወርቅ ተፈትና ፈተናዎችን በድል ትወጣለች፡፡ ጠላቶቿም አፍረው ወደመጡበት ይመለሳሉ፡፡ ዜጎቿ ዛሬ አንገታቸውን ቢደፉም በኢኮኖሚም ቢጎዱም በልማቱ ቀና ብለው የሚሄዱበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም፡፡ የሁለም ዜጎቿ ተስፋ ነው፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://www.press.et/ama/?p=61316

# የእስራኤል የማዕድን ኩባንያ በኢትዮጵያ በተለያዩ የኢንቨስትመንት ዘርፍ ሥራውን ለማስቀጠል ያለውን ቁርጠኝነት አስታወቀ



ዋና መስሪያ ቤቱ በእስራኤል የሆነው ሌካ የተባለው በማዕድን ዘርፍ የተሰማራው ኩባንያ የሥራ ኃላፊዎች ከማዕድን ሚኒስትር ታከለ ኡማ ጋር ምክክር አድርገዋል፡፡

በዚህ ወቅት ሚኒስትሩ ባደረጉት ንግግር ÷ በጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አህመድ አመራር መንግስት ብልጽግናን በሀገራችን ለማስፈን የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ማሻሻያ እርምጃዎችን በቁርጠኝነት ሲወስድ መቆየቱን ጠቁመዋል፡፡

ኢትዮጵያ በፈተና ላይ በምትገኝበት በዚህ ወቅት በግሉ ዘርፍ ኢንቨስትመንት ከፍተኛ ፋይዳ ያለው መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ኢንጅነር ታከለ ÷ "የእስራኤል የማዕድን ኩባንያዎች በዚህ ወሳኝ ወቅት ከኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ጎን ለእውነት ወግናችሁ ስለቆማችሁ ምስጋና ይገባቸኋል" ብለዋል፡፡

በስብሰባው የተገኙት በእስራኤል የኢትዮጵያ አምባሳደር ረታ ዓለሙ ÷ በኢትዮጵያ በማዕድን ልማት ላይ የተሰማሩ የእስራኤል ማዕድን ኩባንያዎችን ተወካዮች በዘርፉ የሚያርጉት እንቅስቃሴ አበረታች መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የኩባንያዎቹ ኃላፊዎች በዚህ ወሳኝ ወቅት ከኢትዮጵያ ጎን እንደሚቆሙ የገለፁ ሲሆን ÷ ስራቸውን አጠናክረው እንደሚቀጥሉም አረጋግጠዋል፡፡

አምባሳደር ረታ ÷ ኢትዮጵያ እና እስራኤል ጠንካራ ታሪካዊ እና መንፈሳዊ ትስስር ያላቸው መሆኑን ጠቁመው ÷ የግሉ ዘርፍ ኢንቨስትመንት በሁለቱ አገራት መካከል ያለውን ወዳጅነት ለማጠናከር ትልቅ አስተዋፅዖ ማበርከት እንደሚችል ማስታወቃቸውን ከእስራኤል የኢትዮጵያ ኤምባሲ ያገኘነው መረጃ ያመለክታል፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://www.fanabc.com/የእስራኤል-የማዕድን-ኩባንያ-በኢትዮጵያ/◦

## ግብር ከፋዮች የታክስ ሕጎችን እየተማሩ መሆኑ ተጠቀሰ

የገቢዎች ሚኒስቴር ከትግራይ ክልል በስተቀር በሁሉም ባሉት አሥር ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶቹ፣ በሳምንት ሁለት ቀናት ለስድስት ሰዓታት መሠረታዊ የታክስ ሕጎች ትምህርት በፓወር ፖይንት (Power Point) መስጠት ጀመረ፡፡

ሚኒስቴሩ እንዳስታወቀው ግብር ከፋዮች 90 ሰዓታት መማር ያለባቸው ሲሆን፣ ፈተናዎችን ካለፉ ሠርተፍኬት ወስደው ራሳቸውንም ከግብር ቅጣቶች ያድናሉ ተብሎ ታስቧል፡፡

«አብዛኞቹ የግብር ቅጣቶች ተደጋጋሚና ባለማወቅ የሚከሰቱ ናቸው፡፡ የ100 ሺሕ ብር ፍሬ ግብር ባለመክፈል የሚሊዮን ብር ቅጣት ይጣልባቸዋል፤» ሲሉ፣ በሚኒስቴሩ የታክስ ከፋዮች ትምህርት ዳይሬክተር አቶ በፍርዱ መሠረት ለሪፖርተር ገልጸዋል፡፡ ከሚቀጥለው ዓመት ጀምሮ የከፍተኛ ደረጃ የታክስ ሕጎች ሥልጠና (አድቫንስድ ሌቭል ትሬኒንግ) ለመስጠት ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን፣ 90 ክሬዲት ሰዓታት የጨረሱ ብቻ ወደዚያ እንደሚያልፉ አስረድተዋል፡፡

አሁን እየተሰጠ ያለው ትምህርት በሦስት የተከፈለ ሲሆን እያንዳንዱ አንድ ወር ከግማሽ ወይም በአጠቃላይ 90 ሰዓት ይፈጃል፡፡ ሦስቱም የቀጥተኛ ታክስና ቀጥተኛ-ያልሆነ ታክስ አስተዳደር ሲሆኑ፣ በአጠቃላይ 13 ሞጁሎች ተዘጋጅተዋል ተብሏል፡፡ በእነዚህ በሦስቱ ምድቦች ውስጥ አሥር ዙሮች እንዳሉ፣ ግብር ከፋዮች አንዱን ዙር በፈተና ሲያልፉ ብቻ ወደ ቀጣይ ዙር ይመዘገባሉ፡፡

ከግንቦት 2013 ዓ.ም. ጀምሮ ሲሰጥ በቆየውና አሁን አሥረኛ ዙር በደረሰው የቀጥተኛ ታክስ ከፋዮች ትምህርት 3,500 ታክስ ግብር ከፋዮች ተፈትነው ማለፋቸው ታውቋል፡፡

«ግብር ከፋዮች እንደ ማንኛውም ተማሪ ተመዝግበውና መታወቂያ ወስደው ተምረውና ተፈትነው ነው የሚያልፉት፡፡ በጣም ብዙ መመርያዎች፣ ደንቦችና አዋጆች በሞጁሎች ውስጥ ተካተዋል፡፡ ትምህርቱን የትልልቅ ድርጅቶች ባለቤቶች፣ አካውንቶቻቸውና የፋይናንስ ኃላፊዎቻቸው እየተማሩ ነው፡፡ ለውጭ ዜጎች በሌሎች ቋንቋዎች ሞጁሎቹ እየተረጎሙ ነው፡፡ ዋናው ትምህርት የትኞቹ ወጪዎችና ገቢዎች በታክስ እንደሚመዘገቡ ማሳወቅ ነው፡፡ በተለይ የንግድ ገቢ ግብር ሕግ ውስብስብ ስለሆነ እሱ ከበድ ብሏቸዋል፤» ሲሉ አቶ በፍርዱ አስረድተዋል፡፡

ሠርተፊኬት የወሰዱ ግብር ከፋዮች አዲስ የግብር ሕግ ካልወጣ በስተቀር ከእንግዲህ የግብር ግንዛቤ ማስጨበጫ ሳያስፈልጋቸው እንደሚከፍሉ፣ ሚኒስቴሩም ራሳቸው አምነው የከፈሉትን የግብር መጠን ኦዲታቸውን ብቻ ቼክ በማድረግ ያረጋግጣል ሲሉ አክለዋል፡፡ ትምህርቱ ተደጋጋሚ የግብር ክስ ጉዳዮች በመብዛታቸው የተጀመረ ቢሆንም፣ በመደበኛ የትምህርት ሥርዓት ውስጥ የታክስ ትምህርት ባለመኖሩ የተፈጠረ ክፍተት ውጤት መሆኑን አስረድተዋል፡፡

ገቢዎች ሚኒስቴር ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመሆን 81 ገጽ ያለው ሰነድ አዘጋጅቶ በመደበኛ ትምህርት ሥርዓት ውስጥ እንዲገባ ያስረከበ ቢሆንም፣ አዲሱ ካሪኩለም ባለፈው ዓመት ይጀመራል ተብሎ በመዘግየቱ፣ ገቢዎች ሚኒስቴር የራሱን ሞጁል አዘጋጅቶ ትምህርቱን መጀመሩን ገልጸዋል፡፡ ትምህርት ሚኒስቴር አፅድቆት የነበረው ሰነድ የታክስ ትምህርት ከቅድመ መደበኛ (ከኬጂ) ጀምሮ እንዲሰጥ ይፈቅዳል፡፡

«ሕፃናት በመጫወቻና በትንንሽ ነገሮች እንዲጀምሩ ተደርጎ ከፍ ሲሉ ግንዛቤያቸው እንዲዳብር ይደረጋል፡፡ ግብር የከፋይ ብቻ ሳይሆን የሁሉም ዜጋ ጉዳይ መሆን አለበት፤» በማለት ዳይሬክተሩ ተናግረዋል፡፡

የክልሎችን ሳይጨምር በፌዴራል ደረጃ የሚታወቁ ወደ 48,000 የሚጠጉ ግብር ከፋዮች መኖራቸውን፣ እየተሰጠ ያለው ትምህርት አስመጪዎችን ባለማካተቱ ለእነሱ ሌላ ሞጁል ከጉምሩክ ኮሚሽን ጋር እየተዘጋጀ ነው፡፡

በአገሪቱ 628 ትልልቅ ግብር ከፋዮች (Large Tax Payer) ሲኖሩ አብዛኞቹ ትምህርቱን እየወሰዱ ነው ተብሏል፡፡ በሚቀጥለው ዓመት የሚጀመረው ትምህርት ዘርፍን መሠረት ያደረገ ሲሆን፣ ለምሳሌ በግንባታ ወይም በቱሪዝም ዘርፍ ያሉ ድርጅቶች ለየብቻ እንደሚማሩ ተጠቁሟል፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://ethiopianreporter.com/article/23919

## የሲሚንቶ ገበያ ሰንሰለት አሻጥር እንዳለበት ተጠቆመ

የሲሚንቶ ፋብሪካዎች ምርቶቻቸውን የሚያከፋፍሉላቸው ወኪል የንግድ ድርጅቶችን ስምና አድራሻ በአስቸኳይ ለመንግሥት እንዲያስታውቁ ታዘዙ፡፡

ትዕዛዙን ያስተላለፈው የማዕድን ሚኒስቴር እንደሆነና ሚኒስቴሩም ይህንን ትዕዛዝ ሊያስተላልፍ የቻለው ከንግድ ሚኒስቴርና ከኢትዮጵያ ኢንቨስትመንትና ኮሚሽን ጋር በመሆን ከሲሚንቶ ምርትና የግብይትና ሥርጭት ሥርዓት ጋር በተያያዘ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመፍታት ለጀመረው የጋራ ጥረት መረጃ ለማግኘት እንደሆነ ሪፖርተር ያገኘው መረጃ ያመላክታል፡፡

«በዚሁ መሠረት የፋብሪካችሁን የሲሚንቶ ምርት በወኪልነት የሚያከፋፍሉ ኩባንያዎች ስም ዝርዝርና የሚገኙበትን አድራሻ በመግለጽ በአስቸኳይ እንድትልኩልን»  ሲል በማዕድን ሚኒስቴሩ ታከለ ኡማ (ኢንጂነር) ተፈርሞ በአገሪቱ ለሚገኙ ሁሉም ሲሚንቶ ፋብሪካዎች የተላከው ደብዳቤ ያመለክታል፡፡

በሲሚኒቶ ምርት ግብይት ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችን የሚፈታ አዲስ መመርያ እስኪዘጋጅ ድረስም ለአዲስ የምርት አከፋፋይ ወኪሎች ፋብሪካዎች ፈቃድ እንዳይሰጡ ደብዳቤው ያሳስባል፡፡

የማዕድን ሚኒስቴር ከኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽንና ከንግድ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በሲሚንቶ ዘርፍ ላይ ከምርት ጀምሮ እስከ ግብይት ሰንሰለቱ ድረስ ያለውን ችግር የተመለከተ ጥናት ያስጠና ሲሆን፣ ባለፈው ዓርብ ኅዳር 17 ቀን 2014 ዓ.ም. የጥናት ሪፖርቱ ላይ መወያየቱ ታውቋል፡፡

የጥናቱ ቡድኑ አባል የሆኑት የማዕድን ሚኒስቴር የሕዝብ ግንኙነት ዳይሬክተር የሆኑት ፍሬሕይወት ፈቃዱ የሲሚንቶ ዘርፉ ከምርት ሒደት እስከ ግብይት ሥርዓቱ ድረስ የሚዘልቁ ችግሮች እንዳሉበት በጥናት መረጋገጡን ለሪፖርተር ገልጸዋል፡፡

በሁሉም ፋብሪካዎች ላይ በተደረገው ጥናት ሁሉም ፋብሪካዎች በሙሉ አቅማቸው እያመረቱ እንዳልሆነ የገለጹት የጥናት ቡድኑ አባል የሁሉም ፋብሪካዎች የምርት መጠን ከአማካይ የማምረት አቅማቸው ከግማሽ በመቶ በታች እንደሆነ ለሪፖርተር ገልጸዋል፡፡

ፋብሪካዎቹ ከአቅም በታች እንዲያመርቱ ያስገደዳቸው ምክንያት፣ የግብይት እጥረት፣ የብድር አለመመቻቸት፣ የማሽነሪዎች መለዋወጫ እጥረትና መሰል ጉዳዮች መሆናቸውን ለጥናት ቡድኑ ማስታወቃቸውን ገልጸዋል፡፡

የሲሚንቶ ምርት እጥረትና የዋጋ ንረት ያለውን ችግር ለመቅረፍ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባው ፋብሪካዎቹ ለሚያነሷቸው ችግሮች መልስ በመስጠት ምርቶቻቸውን እንዲጨምሩ በማድረግ እንደሆነ የሚገልጽ ምክረ ሐሳብ የጥናት ቡድኑ ማቅረቡን ፍሬሕይወት ገልጸዋል፡፡

ከምርት ባለፈ ያለው የግብይት ሥርዓት ጤናማ ባልሆነ የግብይት ሰንሰለት የተዋቀረ መሆኑም በጥናት ቡድኑ መለየቱን ገልጸዋል፡፡ የሲሚንቶ ፋብሪካዎቹ በቀጥታ ለተጠቃሚው መሸጥ እየቻሉ የሲሚንቶ የማከፋፈል የንግድ ሥራ የሚሠሩ ኤጀንቶች ወይም የንግድ ወኪሎች እንዲሁም ቸርቻሪዎች በሚል የተራዘመ የግብይት ሰንሰለት  መፈጠሩ ሌላው ችግር እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

የንግድ ወኪል ተብለው ከፋብሪካዎቹ ጋር የሚሠሩ በአንድ በኩል ቤተሰባዊ ግንኙነት ያላቸው፣ አልፎ አልፎም የፋብሪካዎቹ ከበስተጀርባ የሚታየባቸው መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

በተጨማሪም የንግድ ወኪል ተብለው ሲሚንቶ የሚያከፋፍሉት ድርጅቶች ሕጋዊ ሰውነት ያላቸው ስለመሆኑ የሚያጠራጥሩ ምልክቶች መስተዋላቸውንም ጠቁመዋል፡፡

ኤጀንት ወይም የንግድ ወኪል ተብለው ከፋብሪካ ሲሚንቶ በመረከብ የሚያሠራጩት የንግድ ወኪሎች አሁን ባለው የገበያ ዋጋ ከአንድ ኩንታል ሲሚንቶ ላይ በትንሹ ከ115 እስከ 230 ብር አትርፈው እንደሚሸጡና ከፍተኛ የዋጋ ንረት ተከስቶ በነበረበት ወቅት በፋብሪካው የመሸጫ ዋጋና በኤጀንቶቹ የማከፋፈያ ዋጋ መካከል እስከ 400 ብር የደረሰ ልዩነት መስተዋሉን ጠቁመዋል፡፡

አንድ አንደኛ ደረጃ ወኪል ድርጅት ፋብሪካው ጥሩ ምርት በማረተበት ወቅት በቀን ስምንት የጭነት መኪና ሙሉ ሲሚንቶ በአማካይ እንደሚያገኝ የገለጹት የጥናት ቡድኑ አባል፣ ለአዲስ አበባ እንዲቀርብ የታዘዘ የሲሚንቶ ምርት ወደ ሐዋሳ ተጓጉዞ የሚከፋፈልበትና ከፋብሪካው የወጣ ምርት የት እንደተከፋፈለ የማይታወቅበት ክፍተት በጥናቱ እንደተለየም ገልጸዋል፡፡

ይህንን ችግር ለመፍታትም የጥናት ቡድኑ ሲሚንቶ ምርት ከፋብሪካ አንስቶ ተጠቃሚው ዘንድ እስከሚደርስ ያለውን ሒደት መከታተል የሚያስችል ሥርዓት እንዲዘረጋ ምክረ ሐሳብ ማቅረቡን ገልጸዋል፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://ethiopianreporter.com/article/23884

## ከ32.5 ቢሊዮን ብር በላይ የሚያወጣ ግብይት የተፈጸመ በማስመሰል የተቀናበረ የግብር ሥወራ አሻጥር ተደረሰበት

ከ32.5 ቢሊዮን ብር በላይ የሚያወጣ ግብይት የተፈጸመ በማስመሰል የተቀናበረ የግብር ሥወራ አሻጥር ላይ የተሰማሩ ድርጅቶችና የሚጠቀሙበት ካሽሬጅስተር ማሽን ከነመረጃው በቁጥጥር ሥር ማዋሉን የገቢዎች ሚኒስቴር አስታወቀ።

በሐሰተኛ ማንነት (እውነተኛ ማንነታቸውን በመደበቅ) ያወጡትን የንግድ ፈቃድ ተጠቅመውና አድራሻቸውን ሠውረው ሲንቀሳቀሱ ከነበሩ 63 ድርጅቶች ላይ 20 የካሽሬጅስተር ማሽን ሰሞኑን በቁጥጥር ሥር መዋላቸውን የገቢዎች ሚኒስቴር የኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተር የሆኑት ኡሚ አባ ጀማል ለሪፖርተር ገልጸዋል።

በቁጥጥር ሥር ከዋሉት የካሽሬጅስተር ማሽኖች መረጃዎች መሰብሰባቸውን የገለጹት ኃላፊዋ፣ በተደረገው ምርመራ ከ32.5 ቢሊዮን ብር በላይ የሚያወጣ ግብይት እንደተፈጸመ ተደርጎ ደረሰኝ መቆረጡን ገልጸዋል።

እነዚህ ድርጅቶች በሐሰተኛ ማንነትና አድራሻቸውን በመደበቅ የንግድ ፈቃድ ያወጡ ቢሆንም በንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩ እንዳልሆነ ገልጸዋል።

ዋና ተግባራቸው ሕግን ተከትሎ በወጣ የንግድ ፈቃድ የተገኙ የካሽሬጅስተር ማሽኖችን በመጠቀም ለሚታወቁ ግብር ከፋዮች ወይም የንግድ ድርጅቶች ግብይት እንደተፈጸመ በማስመሰል ደረሰኝ ቆርጦ ማቅረብ ዋነኛ ሥራቸው እንደሆነ ተናግረዋል።

ሐሰተኛ ግብይት እንደተፈጸመ በማስመሰል ደረሰኝ የሚቆርጡት ማንነታቸውን የሠወሩ ድርጅቶች ከሚታወቁ የንግድ ድርጅቶች ጋር በቁርኝት የሚሠሩ መሆኑም በምርመራ መለየቱን ገልጸዋል።

የሚታወቅ የንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩ ግብር ከፋዮች ማንነታቸውን ደብቀው በሥውር ከሚንቀሳቀሱት ድርጅቶች የሚቆረጥላቸውን ደረሰኝ በመረከብ ግብይት እንደፈጸሙ በማስመሰል በዋነኝነት ቫት የሚያጭበረብሩ ሲሆን፣ በዓመቱ መጨረሻ ላይ የሚጠበቅባቸው የገቢ ግብር መጠን ዝቅተኛ እንዲሆንም የሚገለገሉበት መሆኑን አስታውቀዋል።

በዚህ የግብር አሻጥር ከሚፈጸመው ታክስ ማጭበርበር በተጨማሪ የሐሰተኛ ግብይት መረጃውን (ደረሰኙን) በማቅረብ የቫት ተመላሽ ጭምር ከመንግሥት እንደሚጠይቁ ተናግረዋል።

ለሐሰተኛ ግብይቱ የተቆረጠላቸውን ደረሰኝ ተጠቅመው ግብይት እንደፈጸሙ በማስመሰል ከሸማቹ የሰበሰቡትን ቫት በማጣጣት ዜሮ የቫት ሪፖርት ለገቢዎች ሚኒስቴር እንደሚያቀርቡና ከሸማቹ የሰበሰቡትን ቫት ለግላቸው እንደሚያውሉት ወ/ሮ ኡሚ አስረድተዋል።

የተጠቀሰው 32.5 ቢሊዮን ብር ግብይት እውነተኛ ግብይት እንዳልሆነ፣ ነገር ግን ለተጠቀሰው የሐሰተኛ ግብይት መጠን ደረሰኝ የተቆረጠ በመሆኑ ደረሰኙ እጃቸው የገባ ግብር ከፋዮች ታክስ ለማጭበርበር ሊጠቀሙበት እንደሚችሉ ገልጸዋል።

ይህንንም ሲያስረዱ ከተጠቀሰው 32.5 ቢሊዮን ብር ሀሰተኛ ግብይት ውስጥ 15 በመቶ የቫት ምጣኔ ሲሰላ 4.8 ቢሊዮን ብር ቫት ሊጭበረበር እንደሚችል ገልጸዋል።

ለተጠቀሰው መጠን ሀሰተኛ ግብይት የተቆረጡ ደረሰኞች መረጃ በተደረገው ምርመራ የታወቀ በመሆኑ እንዚህን ደረሰኞች ይዘው የሚቀርቡ ወይም በነዚህ ደረሰኞች ተጠቅመው ግብር ያጭበረበሩት ተቋማት በዳግም ኦዲት በቀላሉ ሊገኙ እንደሚችሉ ተናግረዋል።

እንዲህ ዓይነት ግብይት በአብዛኛው የሚከናወነው ግብይታቸውን በደላላ ወይም በማያምኑት ሰው በሚፈጽሙ ግብር ከፋዮች በመሆኑ የንግድ ባለቤቶች ሳያወቁት ወንጀል ውስጥ ተሳትፈው ራሳቸውን እንዳያገኙ ከወዲሁ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ መክረዋል።

ሀሰተኛ ደረሰኝ መጠቀም በግብር አዋጁ ከፍተኛ ቅጣት የሚየስቀጣ ተብለው ከተለዩ የወንጀል ዓይነቶች መካከል አንዱ እንደሆነ የተናገሩት ኃላፊዋ ፤ እስከ አስራ አምስት ዓመት እስራት የሚያስቀጣ ወንጀል መሆኑን ጠቁመዋል።

የተገለጸው መጠንን የያዙት ሀሰተኛ ግበይቶች መረጃ የተገኘው ከ20 የካሽሬጅሰተር ማሽኖች ብቻ እንደሆነም ተናግረዋል።

ይህ ወንጀል የታክስ ስርዓቱ እራስ ምታት እንደሆነም ገልጸዋል።

ከ 2011 ዓም ጀምሮ በተደረገ ክትትል ተመሳሳይ ወንጀል ሲሰሩ የነበሩ ከ400 በላይ ማንነታቸውን የሰወሩ ድርጅቶች መያዛቸውንም ገልጸዋል።

በተያያዘ ዜና ደረሰኝ ሳይቆርጡ ግብይት የፈጸሙ 199 ሰዎች መያዛቸውን የገለጹ ሲሆን ፤ በታክስ አስተዳደር ህጉ መሠረት እያንዳንዳቸው ላይ 50 ሺህ ብር አስተዳደራዊ ቅጣት ፤ በድምሩ በ199 ሰዎች ላይ 1.6 ቢሊዮን ብር ቅጣት መወሰኑን ገልጸዋል።

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://ethiopianreporter.com/index.php/article/24002

## ኢትዮጵያ የአኅዋን ዕድል ብትከለከልም ኢንቨስተሮችን ለመደገፍ የሚያስችል ስትራቴጂ እየተቀረፀ ነው ተባለ

በአሜሪካ መንግሥት የተሰጠው አፍሪካን ግሮውዝ ኤንድ ኦፖርቹኒት አክት (አኅዋ) ዕድል ተጠቃሚነትን ኢትዮጵያ ብትነፈግም፣ ኢንቨስተሮች እንዳይጎዱ የሚያደርግ ስትራቴጂ እየቀረፀ መሆኑን የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን አስታወቀ፡፡

በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል እየተካሄደ ባለው ጦርነት ሳቢያ ሁለቱ አካላት ጦርነቱን በአስቸኳይ የማያቆሙ ከሆነ፣ አገሪቱ ከሃያ ዓመታት በፊት አባል የሆነችበትንና በአገር ውስጥ የሚመረቱ ምርቶችን ወደ አሜሪካ ገበያ ያለ ታሪፍና ኮታ ለመላክ ከአሜሪካ መንግሥት የተሰጣትን የነፃ የገበያ ዕድል፣ እ.ኤ.አ. ጥር 1 ቀን 2022 ጀምሮ ልታጣ እንደምትችል፣ የአሜሪካ መንግሥት መግለጹ ይታወሳል፡፡

የኢንቨስትመንት ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር አቶ ተመስገን ጥላሁን ለሪፖርተር እንደገለጹት፣ ኢትዮጵያን የኢንቨስትመንት መዳረሻ አድርገው የመጡ ኢንቨስተሮችን ለመደገፍ የአጭርና የረዥም ጊዜ ስትራቴጂ እየተዘጋጀ ነው፡፡

ይሁን እንጂ ስትራቴጂው በፖሊሲ ወይም በሕግ ማዕቀፍ ሆኖ እንዲቀርብ የመጨረሻ ውሳኔ እንዳላገኘ በመጠቆም ይፋ ከማድረግ የተቆጠቡት ምክትል ኮሚሽነሩ፣ በአሜሪካ መንግሥት የታቀደው ክልከላ እንዳይፈጸም በሚቀጥሉት 60 ቀናት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ምክክርና ውይይት በማድረግ ውሳኔው ተፈጻሚ እንዳይሆን ጥረት ይደረጋል ብለዋል፡፡

ነገር ግን ውሳኔው ተፈጻሚ የሚሆን ከሆነ በኢትዮጵያ በተለይም በጨርቃ ጨርቅ ዘርፍ ተሰማርተው ምርቶቻቸውን ወደ አሜሪካ ገበያ የሚልኩ ኩባንዎችን ሌላ አማራጭ ገበያ በማፈላለግ፣ እንዲሁም ማበረታቻ በማካተት በሥራቸው ተረጋግተው እንዲቀጥሉ ከድርጅቶቹ ጋር ውይይት መጀመሩን ገልጸዋል፡፡

ኢትዮጵያን ከአኅዋ ተጠቃሚነት መሰረዝ ለጊዜው ኢንቨስተሮችንም ሆነ አገርን ሊጎዳ ቢችልም፣ አገሪቱ በቀጣይ ከሌሎች አገሮች ጋር ሊኖራት የሚችለውን የንግድ ግንኙነት ዘላቂ በሆነ የሕግና የፖሊሲ አሠራር የታገዘ እንዲሆን ዕድል የሰጠ አጋጣሚ ነው ብለዋል፡፡

በተለይም የኢትዮጵያ ምርቶች እንደ አኅዋ ያሉ አማራጭ ገበያዎች በሌሉበት ወቅት፣ ኩባንያዎች ተወዳዳሪ ሆነው በዓለም አቀፍ ገበያ ተመራጭ እንዲሆኑ ትልቅ ሥራ መሠራት እንዳለበት አመላካች እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡

ኢትዮጵን ከተጠቃሚነቱ ለማስወጣት የቀረበውን የአሜሪካ መንግሥት ውሳኔ ተከትሎ ተጠቃሚነቱን ብቻ ታሳቢ አድርገው የመጡ ኩባንያዎች ትንሽ ግራ የመጋባትና ምን ማድረግ እንዳለባቸው ያለ ማወቅ አዝማሚያ እየታየባቸው መሆኑን በመጥቀስ፣ መንግሥት ከእነዚህ ድርጅቶች ጋር ንግግር እያደረገ እንደሆነ ምክትል ኮሚሽነሩ ገልጸዋል፡፡

ምክትል ኮሚሽነነሩ የሰሜኑ ጦርነት ከተጀመረ ወዲህ ወደ ኢትዮጵያ የሚመጣው የኢንቨስትመንት ፍሰት ምንም ዓይነት የመቀነስ አዝማሚያ እንዳላሳየ ቢገልጹም፣ የኮሚሽኑ የ2014 ዓ.ም. የመጀመርያ ሩብ ዓመት አፈጻጸም ከዕቅዱ 60 በመቶውን ብቻ ማሳካት እንደተቻለ ያሳያል፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://ethiopianreporter.com/article/23822

## የግብርና ምርቶች በአግባቡ የሚከማቹበትና የሚጓጓዙበት ቴክኖሎጂ ላይ እየተሠራ መሆኑ ተነገረ

ግብርና ሚኒስቴር ምርትና ምርታማነትን ከመጨመር በሻገር የተመረቱት ምርቶች በአግባቡ በሚከማቹበት፣ በሚቀናበሩበት፣ እንዲሁም እሴት ተጨምሮ ለአገር ውስጥና ለውጭ ገበያ በሚቀርቡበት ቴክኖሎጂ ላይ እየተሠራ እንደሆነ አስታወቀ፡፡

በሚኒስትር ዴኤታ ማዕረግ የግብርና ሚኒስቴር አማካሪ አቶ ወንዳለ ሀብታሙ እንዳስታወቁት፣ በኢትዮጵያ የቀዝቃዛ ሰንሰለት መሠረተ ልማት በበቂ ሁኔታ ባለመኖሩ፣ በተለይም የሆልቲካቸር ምርቶች ወደ ውጭ አገሮች ሲላኩ ችግር ከሚሆንባቸው ውስጥ አንዱ ምርቶቹ ከአንዱ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ እስኪደርሱ የመበላሸት ዕድል ተጋላጭነታቸው ነው፡፡

በመሆኑም በዓለም አቀፍ ደረጃ ሆነ በአገር አቀፍ ደረጃ የኢትዮጵያን ግብርና ምርቶች ወደ ውጭ ኤክስፖርት ሲደረጉ ተወዳዳሪ እንዲሆኑና በአግባቡ የሚከማቹበትና የሚጓጓዙበት ቴክኖሎጂ ወሳኝ እንደሆነ አስታውቀው፣ በተለይም የሆልቲካቸር ምርቶች ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዲገኝባቸው የአትክልትና ፍራፍሬ ማቆያና መጓጓዣ ወደብ ግንባታ ዓይነት ፕሮጀክቶች አስፈላጊ እንደሆኑ አስታውቀዋል፡፡

ለአትክልት፣ ለፍራፍሬና ለሆልቲካልቸር ምቹ የሆነ መሠረተ ልማት ግንባታ ፕሮጀክት ለኢትዮጵያ ከፍተኛ ገቢ የሚያስገኝና በቴክኖሎጂ ሽግግርም ረገድ ትልቅ ለውጥ የሚያመጣ፣ ሰብሎች በብልሽት ሳቢያ የምርት ብክነት እንዳይደርስባቸው በማድረግ ረገድ ሚና የሚጫወትና በአጠቃላይ፣ ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆልቲካቸር ምርት እንድታገኝ የሚያደርግ እንደሆነ አቶ ወንዳለ አስታውቀዋል፡፡

ለአብነትም የአቮካዶ ምርት በኢትዮጵያ በከፍተኛ ሁኔታ እየተስፋፋ ነው ያሉት አቶ ወንዳለ፣ ኢትዮጵያ ከምርቱ ከፍተኛ የሆነ ሀብት እንድታገኝ የቀዝቃዛ ምርቶች ማቆያና ማጓጓዣ መሠረተ ለማቶች ያስፈልጋታል ብለዋል፡፡

በኢትዮጵያ ውስጥ ከአራትና ከአምስት ዓመት በፊት በቂ የሆነ የአቮካዶ ዘር እንዳልነበረ የተናገሩት አማካሪ ሚኒስትር ዴኤታው፣ ‹‹ማሻቭ›› የሚባል የእስራኤል ድርጅት በአሜሪካና በእስራኤል መንግሥት ተረድቶ የአቮካዶ ዘርን በተመለከተ ሥራዎች መከናወናቸውን ተናግረዋል፡፡ በዚህ ወቅት በሁሉም ክልል የአቮካዶ ምርት እየተስፋፋ እንደሚገኝ የተገለጸ ሲሆን፣ ግብርና ሚኒስቴር ምርቱን በአግሪካልቸራል ኮሜርሻላይዜሽን ክላስተር ጭምር በስፋት እያስፋፋ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

በአቮካዶ ብቻም ሳይሆን በሌሎችም ምርቶች ለምሳሌ የቲማቲም፣ የድንች፣ የእንጆሪና ሌሎች ዘጠኝ ዓይነት አጫጭር ፕሮጀክቶችን ጨምሮ ሆልቲካልቸር ምርቶች ላይ ግብርና ሚኒስቴር እየሠራ እንደሚገኝ አቶ ወንዳለ አስታውቀዋል፡፡

በሞጆ ለመሥራት የታቀደው ብሔራዊ የቀዝቃዛ የወደብ ልማት ፕሮጀክት ብቻም ሳይሆን፣ ወደፊት በደቡብ ክልል አርባ ምንጭ፣ እንዲሁም በአማራ ክልል ባህር ዳር ላይ መሰል ፕሮጀክቶች መከናወን አለባቸው ያሉት አማካሪ ሚኒስትር ዴኤታው፣ የተለያዩ ክልሎች እንደ ምርታማነታቸው ሁኔታ እየታየ በጉዳዩ ላይ መሠራት ይኖርበታል ብለዋል፡፡

ግብርና ሚኒስቴር ‹‹ቴን ኢን ቴን›› የሚል በአሥር ዓመት አሥር የተለያዩ የድርጊት አቅጣጫዎች ያሉት ፕሮግራም እንደቀረፀ የተናገሩት አማካሪ ሚኒስትሩ፣ ይህም ቴክኖሎጂ ላይ ምን ይሠራ? ምርታማነት መጨመር ላይ ምን ይሠራ? ፋይናንስ ላይ ምን ይሠራ? የግብርና ሎጂስቲክስ ላይ ምን ይሠራ? የሚሉ በርካታ ጉዳዮች እንዳሉት አስታውቀዋል፡፡

በተጨማሪም ሚኒስቴሩ ምርትን ለመጨመር የሚያስችሉ በርካታ ዘዴዎችን እንደነደፈ የገለጹት አቶ ወንዳለ፣ ይህም ምርትን በበቂ ሁኔታ እንዳይመረት ያደረጉት ጉዳዮች ምንድናቸው? የሚለውን በማጥናት እንደሆነ አስረድተዋል፡፡

ምርትና ምርታማነት መጨመር ብቻውን ትርጉም የለውም ያሉት አማካሪው፣ የተመረተው ምርት የሚከማችበት፣ የሚቀናበሩበት፣ የሚታሸጉበትና ዕሴት የሚጨመርበት ሁኔታ ላይ መሥራት አስፈላጊ እንደሆነ አስታውቀዋል፡፡

በዚህ ወቅት እየተሠራባቸው የሚገኙ የቆላ እርሻ ማስፋፊያዎች፣ የበጋ ስንዴና የመሳሰሉት እንቅስቃሴዎች የግብርና ሥራውን የአርሶ አደሩንና የአገሪቱን ተጠቃሚነት እየጨመሩ ይሄዳሉ ያሉት አቶ ወንዳለ፣ ለአብነትም የሆልቲካቸር ሴክተሩ ከሁለት ዓመት በፊት ከ200 ሚሊዮን ዶላር በላይ የሚያስገኝ እንዳልነበረ አውስተው፣ በተከናወኑ አበረታች ሥራዎች በተጠናቀቀው ዓመት ከዘርፉ 531 ሚሊዮን ዶላር መገኘቱን አስታውቀዋል፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://ethiopianreporter.com/article/23857

## የኢትዮጵያ አየር መንገድ አሸናፊ ሆነ

የኢትዮጵያ አየር መንገድ የ2021 የቢዝነስ ተጓዦች ምርጥ የአፍሪካ አየር መንገድ ሽልማት አሸናፊ መሆኑ ተገለጸ፡፡

በአፍሪካ ግዙፍ የአቪዬሽን ኢንዱስትሪ የሆነው የኢትዮጵያ አየር መንገድ፥ በዓለም አቀፍ ደረጃ ታዋቂ በሆነው ”ቢዝነስ ትራቭለርስ ” መጽሄት የሚያዘጋጀውን ሽልማት ነው በምርጥነት ያሸነፈው።

የዚህ ዓመት ሽልማት የ24 ወራት የደንበኞች ምልከታ የሸፈነ መሆኑ ተገልጿል፡፡

በዚህ ዓመት በንግድ ተጓዦች የተሰጡ ድምጾች፥ የአየር መንገዶችን የተግባቦትና የኮሮና ወረርሽኝ የጥንቃቄ እርምጃዎች ውጤታማነት ታሳቢ ያደረጉ መሆኑም ተገልጿል።

በተሳፋሪዎች አያያዝ፣ በሚጣልበት እምነት እና የቲኬት ለውጦችን በማድረግ ረገድ የሚኖረው ተባባሪነት የወረርሽኙን ጊዜ ታሳቢ ያደረጉ ጥያቄዎች በሽልማት መስፈርትነት መካተታቸውን ኢዜአ ዘግቧል።

ይህ የላቀ ሽልማት የአየር መንገዱ የደንበኞች እርካታ ነጸብራቅ ነው ሲሉ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ተወልደ ገብረማርያም ተናግረዋል፡፡

ሽልማቱ አየር መንገዱ በሁሉም ቦታ የላቀ የደንበኞች አገልግሎት ለማድረስ የሚያደርገውን ጥረት ስኬት የሚያሳይ በመሆኑ የሚያስደስት ነው ብለዋል።

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://www.fanabc.com/የኢትዮጵያ-አየር-መንገድ-የ2021-የቢዝነስ-ተጓ/

## የፈቃድ ብቃት ማረጋገጫ መደቦች ዝቅ ተደረጉ

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር በንግድ አሠራር ላይ ጫና ያሳድራሉ የተባሉትንና ለንግድ ሥራ ፈቃድ ብቃት ማረጋገጫ ይጠየቁ የነበሩ መደቦችን ከ52 ወደ አሥር ዝቅ እንዲሉ ወሰነ፡፡

በአገሪቱ የንግድ ሥራ ለመጀመር እንደ እንቅፋት ሲቆጠሩ የቆዩት እነዚህ ለብቃት ማረጋገጫ ቅደመ መሥፈርት ይጠየቅባቸው ከነበሩ 52 መደቦች ውስጥ 42ቱ ከዚህ በኋላ ማረጋገጫ የማይጠየቅባቸው በመሆኑ በዚሁ መሠረት አሠራሩ ተፈጻሚ እንደሚሆን አስታውቋል፡፡

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር በዚህ ዙሪያ ከዚህ ቀደም ሲቀርብለት የነበረውን አቤቱታ በመመልከት ከኅዳር 6 ቀን 2014 ዓ.ም. ጀምሮ የንግድ ሥራ ፈቃድ ለማውጣት ብቃት እንደ ቅድመ መሥፈርት ይጠየቅባቸው የነበሩ ወደቦችን በመከለስ ወደ አሥር ዝቅ ማድረጉን አስታውቋል፡፡

ከዚህ ቀደም በነበረው አሠራር ብቃት ማረጋገጫ ሲጠየቅባቸውና ተደጋጋሚ አቤቱታዎች ሲቀርብባቸው ከነበሩ የሥራ መደቦች ውስጥ የዕቃ አስተላላፊነት፣ ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭና የኤሌክትሪክ ሥራዎች ተቋራጭ፣ የመርከብ ሥራ ውክልናና የወደብ ሥራዎች፣ የኤሌክትሪክ ሜካኒካል ሥራ ተቋራጮችና የመሳሰሉት መደቦች ይገኙበት እንደነበር ይታወሳል፡፡

ሚኒስቴሩ ባደረገው ማሻሻያ መሠረት እነዚህ መደቦች ከዚህ በኋላ የብቃት ማረጋገጫ የማይጠየቅባቸው እንደሆኑ አሳውቋል፡፡

ይህ ማሻሻያ ከመደረጉ ቀደም ብሎ የብቃት ማረጋገጫ የሚጠየቅባቸው መደቦች በዘርፉ ለመሰማራት ፍላጎት ያላቸው ወገኖች እንዳይሠሩ የሚያደርግ መሆኑን በመጥቀስ ለሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ አቤቱታ ቀርቦ ጉዳዩ ሲታይ መቆየቱ ይታወሳል፡፡

ይህንን የብቃት ማረጋገጫ ይሰጡ የነበሩ 20 የሚደርሱ የብቃት አረጋጋጭ ተቋማት የብቃት ማረጋገጫውን ለመስጠት አሟሉ የሚሉት መሣሪያና ሌሎች መሥፈርቶች ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቁ እንደነበሩ ለማወቅ ተችሏል፡፡

አንዳንድ መሥፈርቶች ደግሞ እስከ 40 ሚሊዮን ብር አስይዙ የሚባልባቸውና ይህንን ለማሟላት ከባድ በመሆኑ በዘርፉ ለመሰማራት ይከብድ እንደነበር ሲገለጽ ቆይቷል፡፡

የብቃት ማረጋገጫው መቅረት አለበት በሚል ለንግድ ሚኒስቴር ማመልከቻ ካስገቡ የተለያዩ የቢዝነስ ዘርፍ ተወካዮች መረዳት እንደተቻለው፣ ብቃት ለማረጋገጥ ይጠየቁ የነበሩ መሥፈርቶች ብዙዎችን አሸሽተዋል፡፡

በሚኒስትር ዴኤታ አቶ ሐሰን መሐመድ ተፈርሞ ህዳር 6 ቀን 2014 ዓ.ም. የወጣው ውሳኔ እንደሚያመለክተው፣ የንግድ ዘርፉን ተልዕኮና ራዕይ ለማሳካት ቀላል፣ ግልጽና ተደራሽነት ያለው አሠራር በማስፈን የቅድመ ንግድ ሥራ ፈቃድ በመሥፈርትነት የሚጠይቀውን የብቃት ማረጋገጫ መደቦች መከለሱ አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበት በዚሁ መሠረት መከለሱን አስታውቋል፡፡

በዚህ የንግድ ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ውሳኔ መሠረት፣ የብቃት ማረጋገጫ ከሚጠየቅባቸው አሥሩ መደቦች ውስጥ የሥጋና የሥጋ ውጤቶች ማቀነባበሪያ፣ የእንስሳት መኖ ማምረቻ ውጤቶች፣ የኬሚካሎች ምርት፣ ለሰው አገልግሎት የሚውሉ የሕክምና ኬሚካሎች ምርት፣ የምግብ ምርቶች አስመጪነት ይገኙበታል፡፡

ከዚህም ሌላ በእንስሳት ሕክምና ሥራዎች የእንስሳት መድኃኒቶችና የሕክምና መገልገያዎችን መሣሪያዎች አስመጪ፣ የእንስሳት መድኃኒት ሕክምና መገልገያዎች አስመጪ ፈቃድ ለማውጣት ብቃት ማረጋገጫ የሚጠየቅባቸው እንደሚሆኑ ያመለክታል፡፡

ቀድሞም ቢሆን የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎትን ለማግኘት ማረጋገጫ ሲጠየቅባቸው ከነበሩ የንግድ ዘርፎች ውስጥ አብዛኞቹ ፈጽሞ የብቃት ማረጋገጫ አያስፈልጋቸውም በሚል ክርክር ሲነሳባቸው ነበር፡፡

በተለይ የዕቃ አስተላላፊነት፣ የመርከብ ሥራ ውክልናና የመደብ ሥራዎች፣ ጠቅላላ ሥራ ተቋራጮችና የኤሌክትሪክ ሥራዎች ተቋራጭ፣ የኤሌክትሮ ሜካኒካል ሥራ ተቋራጮችና የመሳሰሉት የዘርፍ መደቦች ቅድመ ፈቃድ ብቃት መጠየቃቸው አግባብ አይደለም በሚል ለሚኒስቴሩ አቤቱታ ሲቀርብባቸው የነበሩ ዘርፎች ናቸው፡፡

የብቃት ማረጋገጫ መጠየቅ የለበትም የሚል ጥያቄ የያዙ የዘርፉ ተዋናዮች ይህ አሠራር እንዲሻሻል በተደጋጋሚ ጥያቄ በማቅረብ ባለፈው አንድ ዓመት ተኩል ሲሟገቱ ቆይተዋል፡፡

ሚኒስቴሩ እንደ አዲስ ሲደራጅ ይኸው ጥያቄ ቀርቦ በሚመለከታቸው አካላት ከታየ በኋላ 42 መደቦች ማረጋገጫ እንደማይጠየቅባቸው ውሳኔ በማሳለፉ ከትናንት በስቲያ ይህ ውሳኔ ለሚመለከታቸው ሁሉ እንዲደርስ ተደርጓል፡፡

ብቃት አረጋጋጭ መሥሪያ ቤቶችም በዚሁ ውሳኔ መሠረት ተፈጻሚ እንዲያደርጉ በደብዳቤ ተገልጾላቸዋል፡፡

በንግድ አሠራርና ምቹነት ኢትዮጵያ ያለችበትን ደረጃ ለማሻሻልም ይህ ውሳኔ ጠቃሚ ይሆናል ተብሏል፡፡

የዓለም የንግድ ድርጅት አባል ለመሆንም እንዲህ ያሉ የንግድ እንቅስቃሴን የሚገድቡ አሠራሮች መሻሻላቸው አጋዥ ይሆናል፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://ethiopianreporter.com/article/23797

## ረቂቅ ስትራቴጂ ለማፀደቅ ዝግጅት እየተደረገ ነው

የኤክስፖርት ግኝትን ለማሳደግና የወጭ ንግድ ምርቶች ስብጥር ለመጨመር ጉልህ ሚና ይጫወታል የተባለውን፣ የኤክስፖርት ልማትና ፕሮሞሽን ረቂቅ ስትራቴጂ ተጠናቆ እንዲፀድቅ፣ ዝግጅት እየተደረገ መሆኑ ተገለጸ፡፡

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር ዴኤታ አቶ እንዳለው መኮንን ለሪፖርተር በሰጡት መግለጫ፣ በነባር ምርቶች ላይ ልዩ ትኩረት ከመስጠት በተጓዳኝ፣ አዳዲስ ምርቶችን በመለየት ወደ ውጭ ገበያ ማስገባትና አዳዲስ የገበያ መዳረሻዎችን ማስፋትን ዓላማው ያደረገ፣ የኤክስፖርት ልማትና ፕሮሞሽን ረቂቅ ስትራቴጂ በዝግጅት ላይ ነው ብለዋል፡፡

ረቂቅ ስትራቴጂው ተጠናቆ ወደ ተግባር መቀየር ስላለበት፣ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትና የተለያዩ ተቋማት ሚኒስትሮችም ጭምር በተገኙበት ውይይቶችና ገለጻዎች ተደርገዋል፡፡ «ስትራቴጂው እጅግ በጣም ወሳኝ ነው» ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፣ ግብዓቶች ተጨምሮበት በቅርቡ ተጠናቆ ቀርቦ እንዲፀድቅ የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ በጣም ወሳኝ እንደነበር አስታውቀዋል፡፡ በተደረጉ ውይይቶች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር መግባባት ላይ እንደተደረሰም ገልጸዋል፡፡

«ስትራቴጂው በዋናነት የሚያተኩረው ሦስት ጉዳዮች ላይ ነው፡፡ አንደኛው ወደ ውጭ የሚላከውን የምርት ስብጥር ማብዛት (Product Diversification) ሲሆን፣ ይህም አሁን አገሪቱ የምትልካቸውን ምርቶችን ማስፋትን ዋነኛ ሥራ አድርጎ ይወስዳል፡፡ በኤክስፖርት ዝርዝር ውስጥ የሚገኙትን ምርቶችን ማምረት፣ ወይም የሚመረቱትን ማብዛት የሚለው የስተራቴጂው መጀመርያው የትኩረት ጉዳይ ነው፤» ብለዋል፡፡

ሌላኛውና ወሳኝ የሆነው የመዳረሻ አገሮችን መጨመር ወይም ማባዛት (Target Market Diversification) እንደሆነ ያስታወቁት ሚኒስትር ዴኤታው፣ ሦስተኛው ደግሞ የተቋማት አደረጃጀት (Institutional Arrangement) የሚመለከት ነው፡፡ ይህም ከተቋማት ጋር ተያይዞ ምን መድረግ አለበት? በተለይም ከውጤታማነት ጋር ተያይዞ የሚለውን የሚመለከት እንደሆነ አስታውቀዋል፡፡

በረቂቅ ስትራቴጂ ሰነድ ውይይቱ ላይ ኢትዮጵያ የኤክስፖርት ግኝቷን በተፈለገው መጠን እንዳያድግ ካደረጉት ጉዳዮች መካከል የወጪ ንግድ ምርቶች ስብጥር አነስተኛ መሆን፣ ሕገወጥ ንግድ፣ ለጥሬ ዕቃ ግዥ የሚያስፈልግ የውጭ ምንዛሪ እጥረት፣ አገሪቱ ካላት ዕምቅ ሀብት አንፃር የንግድ ሚዛን አለመመጣጠን፣ እንዲሁም የአገር ውስጥ ባለሀብቶች በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ አለመሳተፋቸው ተጠቃሾቹ መሆናቸው ተገልጿል፡፡

የንግድ ሚዛን ለማሻሻልና በኤክስፖርት በሚፈለገው ልክ መነገድና ለአገር ኢኮኖሚ ወሳኝ የሆነውን የውጭ ገንዘብ ለማግኘት እንዲቻል፣ ለረጅም ጊዜ ሲዘጋጅ የቆየው ብሔራዊ የኤክስፖርት ስትራቴጂ ወሳኝ እንደሆነ አቶ እንዳለው አስታውቀዋል፡፡

ብሔራዊ ኤክስፖርት ስትራቴጂ ወሳኝና መሠረታዊ ነው ያሉት አቶ እንዳለው፣ በአጭር ጊዜ ተጠናቆ ተግባራዊ መደረግ እንዳለበትና ይህንንም ወደ ተግባር ለመቀየር መጠነ ሰፊ እንቅስቃሴዎች እየተደረጉ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ስትራቴጂው ወደ ተግባር እንዲገባ ከሚከናወነው ሥራ ጎን ለጎን የዋጋ ማረጋጋትና የመሠረታዊ ሸቀጦች አቅርቦት ሥራ ትኩረት እንደተሰጠው የገለጹት አቶ እንዳለው፣ ስንዴ፣ ዘይት፣ ስኳርና የመሳሰሉ መሠረታዊ ሸቀጦችን ለኅብረተሰቡ የማዳረስ ሥራም ጊዜ የማይሰጠው ስለሆነ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ተለይቶ እንደገና እየተደራጀ ቢገኝም፣ በተጠቀሱት ጉዳዮች ላይ ከሥራ ውጪ ባሉት ቀናትና ሰዓታት ጭምር እየተሠራ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

በዚህ ወቅት አገሪቱ ያለችበት ሁኔታ የሚታወቅ ነው ያሉት አቶ እንዳለው፣ ከጦርነት ባልተናነሰ አጠቃላይ የንግድ ሥርዓቱ ላይ የሚከሰቱ ነገሮች ተገማች ናቸው ብለዋል፡፡ ይህንን አጋጣሚ ተጠቅመው ያላግባብ በሸማቹ ላይ የዋጋ ጭማሪ የሚያደርጉ፣ ከሕገወጥነት ጋር ተያይዞም በሥውር የሚንቀሳቀሱ፣ ኮንትሮባንድን ጨምሮ ሌሎች ሕገወጥ ድርጊቶች ሊከሰቱ የሚችሉበት እንደሆነ አስታውቀው፣ ቁጥጥር ለማድረግ በትኩረት እንደሚሠራበት አስታውቀዋል፡፡

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በዚህ ወቅት ከፍተኛ ትኩረት አድርጎ እየሠራ የሚገኘው የተጀመሩ የሕግ ማዕቀፍ ሥራዎችን ማጠናቀቅ እንደሆነ የተናገሩት አቶ እንዳለው፣ ለአብነትም የቁም እንስሳትን በተመለከተ የተለያዩ ክፍተቶች እንዳሉና ከዚህ ጋር ተያይዞ ራሱን የቻለ መመርያ እየተዘጋጀ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://ethiopianreporter.com/article/23795

## 123 ቢሊዮን ብር ግብር መሰብሰቡን አስታወቀ

በአገሪቱ የተቀሰቀሰው ጦርነት በፈጠረው አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ካለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት የላቀ ነው የተባለ 123 ቢሊዮን ብር ባለፉት አራት ወራት ተሰበሰበ፡፡ ግብር ከፋዮች በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ኃላፊነታቸውን ሳያጓድሉ በመወጣታቸው ገቢዎች ሚኒስቴር አመሠግኗል።

ገቢዎች ሚኒስቴር በአራት ወራት 123.96 ቢሊዮን ብር የሰበሰበ ሲሆን፣ ይህም ከ2013 በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት አፈጻጸፈሙ በ16.3 ቢሊዮን ብር ወይም በ15.2 በመቶ የላቀ ነው ተብሏል።

ሚኒስቴሩ ከሐምሌ 2013 ዓ.ም. እስከ ጥቅምት 2014 ዓ.ም. ባሉት አራት ወራት ውስጥ 133.38 ቢሊዮን ብር ለመሰብሰብ አቅዶ የነበረ ሲሆን፣ የተሰበሰበው 123.96 ቢሊዮን ብር ከዕቅዱ አኳያ ሲመዘን 92.9 በመቶው መሳካቱን ያሳያል።

ይህ ስኬታማ አፈጻጸም ሊመዘገብ የቻለው ግብር ከፋዮች በዚህ አስቸጋሪ ወቅት ሰበቦችን ሳያቀርቡ ኃላፊነት በመወጣቸውና የግብር ሰብሳቢ መሥሪያ ቤቱ ሠራተኞች ከምንጊዜውም በላይ በቁርጠኝነትና ያለ ዕረፍት በመሥራታቸው እንደሆነ ሚኒስቴሩ አመልክቷል።

በአገሪቱ ውስጥ በተፈጠረው ጦርነትና የተለያዩ ግጭቶች ምክንያት አራት ግብር ሰብሳቢ ቅርንጫፎች ምንም ሳይሠሩ፣ ሌሎች ቅርንጫፎችም በተገደበ እንቅስቃሴ ውስጥ ሆነው የተሰበሰበ ገቢ እንደሆነ የሚኒስቴሩ መረጃ ያመለክታል።

«በአገሪቱ በተፈጠረው ጦርነት ምክንያት ገቢን ለመሰብሰብ በማያመች ሁኔታ ውስጥ የተሰበሰበ ገቢ በመሆኑ አፈጻጸሙ የተሻለ ሊባል የሚችል ነው፡፡ በተጨማሪም አፈጻጸሙ በዚህ ወቅት ግብር ከፋዮቻችን ብዙ ሰበቦችን ሳያቀርቡ ለአገራቸውና ለሕዝባቸው በማሰብ በወቅቱና በትክክለኛው ጊዜ ግብራቸውን አሳውቀው በመክፈላቸው እንዲሁም የገቢዎች ሚኒስቴርና የጉምሩክ ኮሚሽን አመራሮችና ሠራተኞችም ከምንጊዜውም በላይ የዕረፍት ጊዜያቸውን ጨምረው በመጠቀምና የገቢ ምንጮችን በዝርዝር በማየት፣ እንዲሁም በቁርጠኝነትና በትጋት ከልብ መሥራት በመቻላቸው የተገኘ ውጤት ነው፤» ብሏል፡፡

በተጠቀሱት አራት ወራት ውስጥ ከተሰበሰበው 123.96 ቢሊዮን ብር ውስጥ 80.8 ቢሊዮን ብሩ የተገኘው ከአገር ውስጥ ታክስ ሲሆን፣ ከውጭ ንግድ ታክስና ቀረጥ ደግሞ 43.1 ቢሊዮን ብር መሆኑን የገቢዎች ሚኒስቴር መረጃ ያመለክታል።

በቀጣይም የተሻለ በመሥራት አገሪቱ ይህንን አስቸጋሪ ወቅት እንድትሻገር የበለጠ ርብርብ እንዲደረግ የገቢዎች ሚኒስቴር ጥሪውን አስተላልፏል።

«ኢትዮጵያውያን ለአገራቸው ሕይወታቸውን ለመስጠት በወሰኑበት በዚህ ጊዜ፣ ግብር ከፋዩ ማኅበረሰብ ለሚወዳት አገሩ ተገቢውን ግብር በተገቢው ጊዜ በመክፈል ግዴታውን እንዲወጣ እያስታወቅን፣ ግብር ከፋዩ ማኅበረሰብ ግብር እንዳይከፍል መቀስቀስና ማሸበር ፈጽሞ ክልክል ነው፤» ሲል የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መምርያ ዕዝ ጥቅምት 26 ቀን 2014 ዓ.ም. ባሳለፈው የመጀመሪያ ውሳኔው ማሳሰቢያ መስጠቱ ይታወሳል።

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://ethiopianreporter.com/article/23829

## የቀዝቃዛ መጋዘን ለመገንባት ዝግጅት እየተደረገ ነው

በግንባታ ላይ በሚገኘው የሞጆ ሁለገብ ሎጅስቲክስ ማዕከል ውስጥ  የቀዝቃዛ መጋዘንና መሠረተ ልማት ለመገንባት የሚያስችል ዝግጅት እየተደረገ ነው፡፡ ይህ የተገለጸው የኢትዮጵያ ማሪታይም ባለሥልጣን የአገሪቱን የሆልቲካቸር የውጭ ምርት ለማሳለጥ የሚያስችል ከአጋር አካላት ጋር በመተባበር የሚተገበር የቀዝቃዛ መጋዘን መሠረተ ልማት የጥናት ሰነድ የሚመለከታቸው የዘርፉ አካላት በተገኙበት ኅዳር 10 ቀን 2014 ዓ.ም. በኢሊሌ ሆቴል በቀረበበት ወቅት ነው፡፡

የጥናት ሰነዱን ደልፊ የተባለ የኔዘርላንድ መንግሥት ድርጅትና ፍላይንግ ስዋን የተባለ ዓለም አቀፍ ድርጅት ሲያቀርቡ በኢትዮጵያ ለሚገኙ ባለድርሻ አካላት ተወካዮችና ኃላፊዎች ጋር ፕሮጀክቱን በቀጣይ ወደ ግንባታ በማስገባቱ ሒደት ላይ ገለፃዎች አድርገዋል፡፡

በማሪታይም ጉዳይ ባለሥልጣን የሎጂስቲክስ ማዕከል ፕሮጀክት ሥራ አስኪያጅ መንግሥት ኃይለ ማርያም (ዶ/ር) ለሪፖርተር እንዳስታወቁት፣ ኩል ፖርት አዲስ የሚባለው ፕሮጀክት (cool Port Addis Project) መነሻው የብሔራዊ ሎጂስቲክስ ስትራቴጂ ነው፡፡

«በኢትዮጵያ ለገቢ ዕቃዎች እንደሚሰጠው ትኩረት ለወጪ ዕቃዎች በሚጠበቀው ልክ ትኩረት አይሰጠውም» ያሉት ሥራ አስኪያጁ፣ የሎጂስቲክስ ስትራቴጂ ጥናት በሚካሄድበት ወቅት የማሪታይም ጉዳዮች ባለሥልጣን ከኔዘርላንድ ኤምባሲ ጋር በነበረው ግንኙነት ክፍተቶቹን ለመሸፈን ከታሰቡት ነገሮች አንዱ የቀዝቃዛ መጋዘን መሠረተ ልማት ፕሮጀክት እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

«ኩል ፖርት አዲስ» በሞጆ የአረንጓዴ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክት ውስጥ ከሚካተቱ አንዱ ፕሮጀክት እንደሆነ ያስታወቁት መንግሥት (ዶ/ር)፣ ግንባታው በተጀመረው የሞጆ ሎጂስቲክስ ማዕከል ውስጥ እንደ አንድ መሠረተ ልማት ኢትዮጵያ ያላትንና በበቂ ደረጃ ያልጠቀመችበትን የሆልቲካቸር ምርቶች እንድትጠቀም የሚያደርግ እንደሆነ አስታውቀዋል፡፡

ፕሮጀክቱ እ.ኤ.አ. ከ2015 ጀምሮ የቅድመ አዋጭነት ጥናት በማሪታይም ጉዳዮች ባለሥልጣን አማካይነት ተሠርቶለት እንደነበር የተገለጸ ሲሆን፣ በመቀጠልም በኢትዮጵያና  በኔዘርላንድ መንግሥታት መካከል ፕሮጀክቱን ለመተግበር ከፍተኛ ተነሳሽነት ተፈጥሮ  የጋራ መግባቢያ ሰነድ ከሦስት ዓመት በፊት ተፈርሞ ነበር፡፡

ፕሮጀክቱ በዚህ ወቅት የትግበራና የፋይናንስ አዋጭነት ጥናቶች ተሟልተውለት የቀረበ እንደሆነ የተገለጸ ሲሆን፣ ከግብርና ሚኒስቴር አንስቶ የምድር ባቡር ኮርፖሬሽን፣ ከሎጂስቲክስ ትራንስፎርሜሽን ቢሮ የተውጣጡ ቴክኒካል ቲሞቻና ባለሙያዎች አስተያየት ሰጥተውበት የዳበረ እንደሆነ ተገልጿል፡፡

ፕሮጀክቱ በ50 ሚሊዮን ዶላር በሦስት ምዕራፍ የሚፈጸም እንደሆነ ያስታወቁት መንግሥት (ዶ/ር)፣ የፕሮጀክቱን አስተዳደር በተመለከተ በጥምረት (Joint Venture) ከማስተዳደር አንስቶ የተለያዩ አማራጮች እንደተቀመጡ አስታውቀዋል፡፡

በሞጆ የሎጂስቲክስ ማዕከል የሚገነባው የቀዝቃዛ መጋዘን መሠረተ ልማት ከሚገነባበት አካባቢ አንስቶ፣ ጂቡቲ ደርሶ ወደሚፈለገው አገር ምርትን ለመላክ በሚደረገው እንቅስቃሴ ውስጥ፣ በተለይም በማንኛውም ኮንቴይነር ውስጥ የማይጓጓዙትን የሆልቲካቸርና ተዛማጅ ምርቶች ለመላክ የሚያስችሉ መሠረተ ልማቶች ግንባታን የሚያጠቃልል ነው፡፡ ይህም የባቡር መሠረተ ልማት፣ የወደብ ማሽነሪዎችና የተለዩ ኮንቲይነሮችንና የቀዝቃዛ መጋዘን የሚጠቀም ነው፡፡

በኢትዮጵያ ማሪታይም ባለሥልጣን የሎጂስቲክስ ትራንስፎርሜሽን ጽሕፈት ቤት ምክትል ዳይሬክተር አቶ እውነቱ ታየ በሌላ በኩል እንዳስታወቁት፣ የቀዝቃዛ ማጓጓዣ አገልግሎት ለማከናወን ከሚያስፈልጉ የሎጂስቲክስ ሠንሠለት ሥራዎች አንዱ ይህ ጥናት ነው፡፡

የኢትዮጵያ ማሪታይም ባለሥልጣን ፕሮጀክቱን በተመለከተ የማስተባበር፣ ፈንድ የማፈላለግ ኃላፊነትን እንደወሰደ የተገለጸ ሲሆን፣ ሞጆ ላይ የሚገነባው የቀዝቃዛ ሠንሠለት መሠረተ ልማት ወደ አዲስ አበባ የግብይት ማዕከላት ከሚያቀርባቸው ምርቶች ባሻገር ወደ ውጭ ቀጥታ ለቀዝቃዛ ምርቶች ተብለው በተዘጋጁ ኮንቴይነሮች የሚልክ እንደሆነ ተገልጿል፡፡

ፕሮጀክቱ በአገሮቹ መልካም ፍቃድ የሚተገበር እንደመሆኑ መጠን የራሱ የትግበራ አካሄድ እንዳለው የተገለጸ ሲሆን፣ ሆኖም ጥናቱን ያከናወኑት የኔዘርላንድ መንግሥትና ኩባንያ ከዓመት በኋላ ፕሮጀክቱን የመተግበር ዕቅድ እንዳላቸው መንግሥት (ዶ/ር) ተናግረዋል፡፡

አገሪቱ የአቮካዶ ምርት ወደ ውጭ አገሮች መላክ እንደመጀመሯ መጠን ይህ ፕሮጀክት በቶሎ መጀመሩ የተጀመረውን እንቅስቃሴ ለማጠናከር ጉልህ አስተዋጽኦ እንደሚኖረውና በኢትዮጵያም በኩል ከፍተኛ ተነሳሽነት እንዳለ በመድረኩ ተገልጿል፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

ttps://ethiopianreporter.com/article/23831

ዋና አዘጋጅ፡-

ደበበ አበበ

አዘጋጅ፡-

ዮሴፍ ተሾመ


አድራሻ፡-

ስልክ-፡- +251-115-54-09-93

ፋክስ፡-+251-011-5517699

ድረ-ገጽ፡-
www.ethiopianchamber.com

Facebook:
https://www.facebook.com/EthiopianChamber

Twitter:
https://twitter.com/EthiopiaChamber

Telegram:
t.me/ethiopiachamber


## ECCSA Resource Center

Ethiopian Chamber of Commerce & Sectoral Associations (ECCSA) Resource Center has stated giving service to member. The center is located at the head quarter of ECCSA.

It is a unit dedicated to serve the business community, its members and staffs with a range of timely and cost-effective information services which will enhance the decision-making process and competitiveness of the chamber system management and the business community.

It is also a WTO (World Trade Organization) Reference Center for the private sector, to enable business community to access online trade data and WTO-related documents on a continuous basis, to help identify market niches for the export of their products and services.

The center works on the principle of the 5Rs: providing the Right information to the Right person at the Right time in the Right quantity and Right quality.

The Center's Services

Reference, Resources Loan & Interlibrary Loan Services

Internet & Electronic Resource Services

Support on information searching

Reprographic Service

Advising users on reference materials available in resource center.

Types of Materials in the Center

Books, Periodicals, Journals, Magazines

Audio and Video CD collections

E-Books & Publications

Business & Economic Statistics & Databases

Access to international organization's online information (WTO, ITC, UNCTAD, World Bank, PACCI, WCO, etc.)

For further information:

Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Associations

ECCSA Resource & WTO Reference Center

Mexico Square, ECCSA Building

Ground Office , Room No. 13/14

Open to public Monday-Friday from 2:30 am to 5:00 pm

Tel: 251-115514005

Mob. 0966038499

Fax: 251-115517699

## የግልግል አገልግሎት



የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት በማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 341/95 አንቀጽ 5(6) መሰረት በንግድ ማህበረሰቡ መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን እንዲፈታ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡ በዚህም መሰረት አለመግባባቶችን በፈጣን እና ሚስጥራዊነቱ በተጠበቀ ሁኔታ እንዲፈታ ከማድረጉም በላይ ለባለ ጉዳዮች አመቺ እንዲሆን ቅዳሜንም ጨምሮ ዓመቱን ሙሉ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡
በመሆኑን የዚህ አገልግሎት ተጠቃሚ እንድትሆኑ ስንጠይቅ የንግድ ማኅበረሰቡን ለማገልገል ያለንን ቁርጠኝነት በመግለጽ ነዉ፡፡

ለበለጠ መረጃ ፡- ሜክሲኮ አደባባይ በሚገኘዉ የንግድ ምክር ቤት ሕንጻ 1ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 15 በአካል በመቅረብ
ወይም
በስልክ ቁጥር +251 115 311015 በመደወል ማነጋገር ትችላላችሁ፡፡

**የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት**
**የግልግል ማዕከል**